
# መጽሐፈ ፍልስፍና



@ETHIO_PDF_BOOKS

Ar-552

# ሐተታ ዘርአያቆብ

ከመጀመሪያዎቹ
የአፍሪካውያን ፍልስፍናዎች አንዱ

## ኢትዮጵያዊ ፍልስፍና

Sca

# ዘርአያቆብ ኢትዮጵያዊው ፈላስፋ

የመጀመሪያውና ብቸኛው ኢትዮጵያዊ ፈላስፋ በ1640 ግድም የፃፈው ይህ መፅሀፍ ለረዥም ዓመታት ፀሐፊው ኢትዮጵያዊ አይደለም ጣሊያናዊ መነኩሴ እንጂ በሚል ከፍተኛ ክርክር ያስነሳ ቢሆንም ዛሬ እንደ ቴዎድሮስ ኪሮስ አባባል ኢትዮጵያዊነቱ ተረጋግጧል። ይህ መጽሃፍ በተለያዩ ጥራዞችና ቋንቋዎች በአለም በሙሉ እስከ ዛሬ የሚታተም ሲሆን በአገራችን በዘመንፈስ ቅዱስ አብርሃ ጥረት ከታተመ ወደ 50 ዓመታት አልፈውታል።

ይህ ልዩ የሆነ አስተሳሰብ ከኢትዮጵያውያን ጭንቅላት ሊፈልቅ አይችልም። እስከ ማለት የደረሰው ጣሊያናዊ ኮንቲ ሮሲኒ የተለያዩ የተምታቱ ማስረጃዎችን በመደርደር ኢትዮጵያውያንን ለማንኳሰስ ሞክሮአል። የዚህ ሰው ፅሁፍ ሲታይ የኔታ አለማየሁ ሞገስ በምላሻቸው እንደጠቀሱት ጣሊያን በአድዋ የደረሰባትን ሽንፈት ለመበቀል ከወሰደቻቸው እርምጃዎች አንዱ አካል ነው። ለመከራከሪያ ያቀረበውን ፅሁፍ መዝጊያ ማየት ብቻ ለዚህ በቂ ማስረጃ ሊሆን ይችላል።

የ"መጽሃፈ ዘርአ ያዕቆብ" እና ከዚሁም የ"መጽሐፈ ወልደ ሕይወት"
ደራሲው መሆኑን በማወቅ ቂሙን
የምወጣ መሆኑን መቸም አላስበውም
ነበረ። ግን የ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን
ዕንቁ ይመስል የነበረው "ከኢትዮጵያ ሥነ
ጽሁፍ በንኖ ሲሄድ በማየቱ ከልቤ
እያዘንኩ ነው። "

አንባቢ ያቀረባቸውን ማስረጃዎችና ሃተታዎች አገናዝቦ የራሱን አቋም ለመውሰድ ይችል ዘንድ የኮንቲ ሮሲኒን ሙሉ ፅሁፍ አቅርበናል፡፡ ለዚህ አይን ያወጣ ዝርፊያ በሰፊውና ዘርዘር ባለ መልኩ ተቃውሞ ያቀረቡ የኔታ አለማየሁ ሞገስ ናቸው፡፡ ፅሁፉ ሰፊ በመሆኑ በተለይ ግዕዙንና አንዳንድ በቀላሉ ሊገለፁ የማይችሉትን ቀንሰን አሳጥረን አቅርበነዋል፡፡

ከዚህ ውጭ የዘመኑን አንዳንድ ምሁራን በተለይ ከጉዳዩ ጋር ቅርበት ያላቸውን ለማነጋገር ሞክረን አብዛኛዎቹ የኮንቲ ሮሲኒን ሃሳብ ወደ መቀበሉ ያዘነበሉ መሆናቸውን በመረዳታችን እፍረትም ሃዘንም ተሰምቶናል፡፡

ይህ መጽሐፍ ኢትዮጵያዊ በሙሉ ሊያየው ሊያነበውና ሊመረምረው ይገባል ብለን እናምናለን፡፡ ስለዚህም ለዘመኑ ወጣቶችና ሳያነቡት ላለፉት ጎልማሶችና አዛውንት ይደርስ ዘንድ እነሆ ታተመ፡፡

ዳንኤል ወርቁ ካሳ

# ሀተታ ዘርአ ያቆብ

እግዚአብሔርን የምትፈሩ ሁሉ ለነፍስ ያደረጋላችሁን መናገር እጀምራለሁና ኑ ስሙኝ:: ሁሉን በፈጠረ መጀመሪያና መጨረሻ በሆነ ሁሉን በያዘና የህይወትና የጥበብ ሁሉ ምንጭ በሆነ እግዚአብሔር በሰጠኝ ረዥም እድሜዬ ካጋጠመኝ ትንሽ እፅፋለሁ:: ነፍሴ በእግዚአብሔር ዘንድ የተባረከች ትሁን ገሮችም ሰምተው ይደሰቱ:: እኔ እግዚአብሔርን ፈለኩት መለሰልኝ:: አሁንም እናንተ ወደ እርሱ ቅረቡ ያበራላችሁማል ፊታችሁንም አያሳፍርም:: እግዚአብሔርን ከእኔ ጋር ከፍ ከፍ አድርጉት አብረን ስሙን እናንሳ:: እኔ የተወለድኩት በአክሱም በካህናት አገር ነው:: ነገር ግን እኔ በአክሱም አውራጃ አዬ ዘርአ ያቆብ በነገሠ በሶስተኛው ዓመት በ1592 ዓ.ም ከአንድ ገበሬ ቤተሰብ ተወለድሁ:: በክርስትና ጥምቀት ዘርአ ያቆብ ተብዬ ተሰየምኩ:: ሰዎች ግን ወርቄ ይሉኛል:: ካደኩ በኋላ ትምህርት እንድማር አባቴ ወደ ትምህርት ቤት ላከኝ:: ዳዊትም ከደገምኩ በኋላ መምህሬ አባቴን ይህ ህፃን ልጅህ ልቦናው የበራ በትምህርት ታጋሽ ነውና ወደ ትምህርት ቤት ብትልከው ሊቅና መምህር ይሆናል አለው:: አባቴም ይህን ሰምቶ ዜማ እንድማር ላከኝ:: ሆኖም ድምፄ ሸካራ ሆኖ አላምር አለኝ:: በዚህም ምክንያት ጓደኞቼ መሳቂያና መዘባበቻ አደረጉኝ:: እዛም ሦስት ወር ያህል ቆየሁ:: ስላልተሳካልኝ ከልቤ አዘንኩ:: ተነስቼ ሰዋሰውና ቅኔ ለመማር ወደ ሌላ አስተማሪ ሄድኩ:: ከጓደኞቼ ፈጥኜ እንድማርም እግዚአብሔር ጥበቡን ሰጠኝ:: ይህም የመጀመሪያ ሃዘኔን አስረሳኝ::

በጣም ተደሰትኩ። እዛም አራት አመት ቆየሁ። በነዚያ ቀኖች እግዚአብሔር ከሞት አዳነኝ። ከጓደኞቼ ጋር ስጫወት ወደ ገደል ወደኩ። እግዚአብሔር በታምራቱ አዳነኝ እንጂ ፈፅሞ ልድን አልችልም ነበር። ከዳንኩ በኋላ ገደሉን በረጅም ገመድ ለካሁት። አስራ ሦስት ሜትር ሆኖ ተገኘ። እኔም ድኜ ያዳነኝን እግዚአብሔር እያመሰገንኩ ወደ መምህሬ ቤት ሄድኩ። ከዚያም ተነስቼ የቅዱሳት መፃህፍትን ትርጓሜ ለመማር ሄድኩ። በዚያም አሥር አመት ቆየሁ። መጽሐፍትን ፈረንጆች እንዴት እንደሚተረጉሟቸው የኛም ምሁራን እንዴት እንደሚተረጉሟቸው ተማርኩ። ትርጓሜያቸው ግን ከኔ ልቦና ጋር የሚስማማ አልነበረም። ሆኖም ይህን ስሜቴን ሀሳቤን ለማንም ሳልገልፅ በልቤ ይገኛው ቆየሁ። ከዚያም ወደ አገሬ ወደ አክሱም ተመለስኩ። በአክሱም ለአራት አመት መፅሐፍ አስተማርኩ። ይህ አመት ክፉ ዘመን ሆነ። አፄ ሱስንዮስ በነገሰ በ19ኛው አመት የፈረንጆች ተወላጅ አቡነ አልፎንዝ መጣ። ከሁለት አመት በኋላም ንጉሱ የፈረንጆችን ሃይኖማት ስለተቀበለ በኢትዮጵያ ትልቅ ስደት ሆነ። ይህን ሃይማኖት ያልተቀበለው በሙሉ ግን እጣው ስደት ሆነ።

## አፄ ሱስንዮስ፣ አልፎንዝና ጠላቴ ወልደ ዮሐንስ

እኔ በሀገሬ መፃሕፍትን ሳስተምር ብዙዎቹ ጓደኞቼ ጠሉኝ። በዚህ ዘመን የባልንጀራ ፍቅር ጠፍቶ ነበርና ቅናት ያዛቸው። በትምህርትና ጓደኛን በመውደድ ከነርሱ እበልጣለሁ። ከሁሉ ሰው፣ ከፈረንጆቹና ከግብፃውያን ሁሉ ጋ እስማማለሁ። መጽሐፍን ሳስተምርና ስተረጉም ካቶሊኮች እንዲህ እንዲህ ይላሉ። ግብፃውያኖች ደግሞ (ኦርቶዶክሶች) እንዲህ እንዲህ ይላሉ እላለሁ። እኛም ብንመረምር ይህን ሁሉ እናውቃለን እላለሁ እንጂ ይህ መልካም ነው ይህ ደግሞ ክፉ ነው አልልም። ግብፃውያኖች የፈረንጅ፣ ፈረንጆቹ ደግሞ የግብፃውያኖቹ እመስላቸዋለሁ። ስለዚህ ሁሉም ጠሉኝ። ብዙ ጊዜም ወደ ንጉሡ ከሰሱኝ። እግዚአብሔር ግን አዳነኝ። ከዚህም በኋላ ከአክሱም ካህናት አንድ ወልደ ዮሐንስ የተባለ ጠላቴ የንጉስ ወዳጅ ስለነበረ፣ የነገስታት ፍቅር በሸንገላ ምላስ ስለሚገኝ ወደ ንጉሱ ሄደ። ወደ ንጉሱም ገብቶ እንደዚህ አለው።

"ይህ ሰው ህዝብን ያሳስታል። ስለሃይማኖታችን እንነሳና ንጉሱን እንግደለው፣ ፈረንጆቹንም እናባራቸው ይላል" እያለ ይሄንና ይህን በመሰለ ውሸት ከሰሰኝ። እኔም ይህን አውቄ ገና ለገና ይገድለኛል ብዬ ፈርቼ የነበረኝን ሶስት ወቂት ወርቅና የምፀልይበትን መዝሙረ ዳዊት ይዤ በሌሊት ሸሸሁ። ወዴት እንደምሄድ ለማንም አልነገርኩም። ወደ ተከዜ በረሀ ገባሁ። በነጋታው ራበኝ። ከሀብታሞች ገበሬዎች እንጀራ ለመለመን እየፈራሁ ወጣሁ። ሰጡኝና በልቼ እየሮጥኩ ሄድኩ። እንዲህ እያልኩ ብዙ ቀን ቆየሁ፣ በኋላ ወደ ሸዋ ግድም ስሄድ

ሰው የሌለው በረሀ አገኘሁ። ከገደሉ በታች መልካም ዋሻ ነበርና ሰው ሳያየኝ በዚህ ዋሻ እኖራለሁ ብዬ ወሰንኩ። ሉስንዮስ እስኪሞት ድረስ በዚያ ሁለት አመት ቆየሁ። አንዳንድ ጊዜ ወደ ገበያ እየወጣሁ ወይም ወደ አማሮች አገር እሄድ ነበር ለአማራ ሰዎች የምበላው እንዲሰጡኝ የምለምን ባህታዊ መነኩሴ እመስላቸው ነበር። ነገር ግን ሰዎች ከየት እንደምመጣ ወዴት እንደምገባ አያውቁም። በዋሻዬ ሉብቻዬ በሆንኩ ጊዜም በመንግስተ ሰማያት የምኖር መሰለኝ። ቁጥር የሌለው ክፋታቸው አውቄ ከሰዎች ጋር መኖርን ጠላሁ። ሌሊት መጥተው የበረሀ አራዊት እንዳይበሉኝም በድንጋይና በአሸዋ አጥር ዋሻዬን አጠርሁ። እሚፈልጉኝ ሰዎች ወደ እኔ ቢመጡ የማመልጥበት መውጫ አዘጋጀሁ። እዛ በሰላም ኖርኩ። በሚሰማኝ በእግዚአብሔር ተስፋ አድርጌ በሙሉ ልቤ በመዝሙር ዳዊት ፀለይኩ።

## ስለ አምላክ መኖርና የሐይማኖት መለያየት

ከፀሎትም በኋላ ሥራ ስለሌለኝ ሁልጊዜ ስለሰዎች ክፋትና ሰዎች በእርሱ ስም ሲበድሉ፣ ወንድሞቻቸውን ጓደኞቻቸውን ሲያባርሩ እና ሲገድሉም ዝም በማለቱ ስለፈጣሪ ጥበብ አስብ ነበር። በዚህም ጊዜ ፈረንጆቹ አየሉ። ነገር ግን ያገሩ ሰዎችም ከነሱ የባሰ ክፋት ሰሩ እንጂ ፈረንጆቹ ብቻቸውን አልነበረም የከፉት። የካቶሊክ ሃይኖማት የተቀበሉት ኦርቶዶክሶች የመንበረ ጴጥሮስን እውነተኛዋ ሃይማኖት ክደዋልና የእግዚአብሔር ጠላቶች ናቸው አሉ። ስለዚህም

አሳደዷቸው። አርቶዶክሶችም ለሃይማኖታቸው እንዲሁ አደረጉ።

እግዚአብሔር የሰዎች ጠባቂ ከሆነ ለምን ፍጥረታቸው እንዲህ ከፋ ብዬ አሰብኩ። በአርያም የሚያውቅ አለን? ኧረ እግዚአብሔርስ ያውቃልን? በቅዱስ ስሙ ሲበድሉና ስሙን ሲያረክሱ የሚያውቅ ከሆነ እንዴት የሰዎችን ክፋት ዝም ይላል አልኩ። ምንም ልብ አላደረኩምና ብዙ አሰብኩ። የፈጠርከኝ ፈጣሪዬ ሆይ አዋቂ አድርገኝ፣ የተደበቀውን ጥበብህን ንገረኝ ብዬ ጸለይኩ። ለሙት እንዳይተኙ አይኖችህን አብራቸው። እጆችህ አደረጉኝና ሰሩኝ። ትዕዛዛትህን እንድማር ልብ ስጠኝ። ለኔ ግን እግሮቼ በተፍገመገሙ፣ ተረከዞቼም በተንሸራተቱ ነበር። ይህም በፊቴ ስላለው ድካም ነው። ይህንንና ይህን የመሰለ ፀሎት አደርግ ነበር። አንድ ቀን እኔ ወደ ማን ነው የምፀልየው አልኩ። በእውነት የሚሰማኝ እግዚአብሔር አለን? በዚህም አሳብ በጣም አዝኜ እንዲህ አልኩ። ዳዊት እንዳለ እንዴት ምንኛ ልቤን በከንቱ አፀደኳት። ኋላም አሰብኩ ይህ ዳዊት እንዲህ የሚለው ጆሮን የተከለ አይሰማምን? በእውነት እንድሰማበት ጆሮ የሰጠኝ ማነው? አዋቂስ አድርጎ የፈጠረኝ ማነው? ወደዚህስ አለም እኔ እንደምን መጣሁ? ከወዴትስ መጣሁ? ከዓለም በፊት ብኖር የህይወቴ መጀመሪያና የእውቀቴ መጀመሪያን ባወኩ። እኔ በገዛ እጄ ተፈጠርኩን? ነገር ግን እኔ በተፈጠርኩ ጊዜ አልኖርኩም። አባትና እናቴ ፈጠሩኝ ብልም እንደገና ወላጆችና የወላጆችን ወላጅ፣ ወላጅ የሌላቸውን በሌላ መንገድ ወደዚህ አለም የመጡትን እንደኛ

ያልተወለዱትን የፊተኞቹ ድረስ ፈጣሪያቸውን አፈልጋለሁ። እነርሱም ቢወልዱ የፈጠራቸው አንድ ሀላዊ አለ ከማለት በቀር የጥንት መወለጃቸውን አላውቅም። ያለና በሁሉም የሚኖር የሁሉ ጌታ ሁሉን የያዘ መጀመሪያና መጨረሻ የሌለው አመቱ እማይቆጠርና እማይለወጥ ያልተፈጠረ ፈጣሪ አለ አልኩ። ፈጣሪስ አለ። ፈጣሪ ባይኖር ፍጥረት ባልተገኘ አልኩ። እኛ ብንኖር ፍጡራን እንጂ ፈጣሪዎች አይደለንም። የፈጠረን ፈጣሪ አለ እንል ዘንድ ይገባናል። ይህም የፈጠረን ፈጣሪ አዋቂና ተናጋሪ ካልሆነ በቀር ከእውቀቱ በተረፈ አዋቂዎችና ተናጋሪዎች አድርጎ ፈጥሮናል። ሁሉን ፈጥሯል ሁሉን ይይዛልና እርሱ ሁሉን ያውቃል። ፈጣሪዬ ወደ እርሱ ስፀልይ ይሰማኛል ብዬ ሳስብ ትልቅ ደስታ ተደሰትኩ። በትልቅ ተስፋም እየፀለይኩ ፈጣሪዬን በሙሉ ልቤ ወደድኩት። ጌታዬ ሆይ አንተ ሀሳቤን ሁሉ ከሩቅ ታውቃለህ አልኩት። አንተ የመጀመሪያዬ ነህ። የመጨረሻዬን ሁሉን አወቅህ። መንገዴንም ሁሉ አንተ አስቀድመህ አወቅህ። ስለዚህ ከሩቅ ታውቃለህ ይሉሀል። እኔ ሳልፈጠር ሀሳቤን ያውቃልና ፈጣሪዬ ሆይ እውቀትን ስጠኝ አልኩ።

## ስለ ሃይማኖት ምርመራና ፀሎት

በኋላም ይህ በቅዱሳት መፃሕፍት የተፃፈ ሁሉ እውነት ይሆን? ብዬ አሰብኩ። በጣም አላወኩምና የተማሩና ተመራማሪ ሰዎች እውነትን እንዲነግሩኝ ሄጄ ልጠይቃቸው ብዬ ብዙ አሰብኩ፤እንደገናም ሰዎች በየልባቸው ያለውን ካልሆነ በቀር ሌላ ምን

ይመልሱልኛል ብዬ አሰብኩ። ሰው ሁሉ የኔ ሃይማኖት እውነተኛ ናት ይላል። በሌላ ሃይማኖት የሚያምኑ ሐሰተኞች የእግዚአብሔር ጠላቶች ናቸው። ዛሬም ቢሆን ፈረንጆች ሃይማኖታችን መልካም ናት፤ሃይማኖታችሁ ግን መጥፎ ናት ይሉናል። እኛም መልሰን እንደዚህ አይደለም የናንተ ሃይማኖት መጥፎ የኛ ሃይማኖት ግን መልካም ናት እንላቸዋለን። እንደገናም የእስልምና፣የአይሁድ አማኞችን ብንጠይቃቸው እንዲሁ ይሉናል። በዚህም ክርክር ፈራጅ ማን ይሆናል። ሰዎች ሁሉ እርስ በእርሳቸው ወቃሾችና ተወቃሾች ሆነዋል። አንድ እንኳን ከሰው ልጅ የሚፈርድ አይገኝም። እኔ መጀመሪያ ስለ ብዙ ሃይማኖቶች ጉዳይ አንድ ፈረንጅ መምሕር ጠየኩ። እሱ ግን ሁሉን እንደ ራሱ ሃይማኖት አድርጎ ፈታው። ኋላም አንድ ትልቅ የኢትዮጵያ መምህር ጠየኩ። እርሱም ሁሉንም እንደ ሀይማኖቱ አድርጎ ተረጎመው። እስልምናና አይሁድንም ብንጠይቅ እንዲሁ እንደ ሃይማኖታቸው ይተረጉማሉ። ታድያ እውነት የሚፈርድ የት አገኛለሁ? የኔ ሃይማኖት ለእኔ እውነት እንደሚመስለኝ እንዲሁ ሌላውም ሃይማኖቱ እውነት ይመስለዋል። ነገር ግን ፅድቅ አንዲት ብቻ ናት።

እንደዚህ እያልኩ አሰብኩ። ጠቢብና የእውነተኞችም እውነተኛ እኔን የፈጠርክ ሆይ አዋቂ አድርገህ የፈጠርከኝ ሆይ ዳዊት ሰው ሁሉ ዋሾ ነው ካለው በስተቀር በሰው ዘንድ ጥበብና እውነት አይገኝምና አንተ አዋቂ አድርገኝ ብዬ ፀለይኩ። ሰዎች በዚህ ትልቅ ነገር ነፍሳቸውን ለማጥፋት ስለምን ይዋሻሉ? ብዬ

አሰብኩ። የሚዋሹም መሰለኝ። የሚያውቁ እየመሰላቸው ምንም አያውቁምና የሚያውቁ ይመስላቸዋል። ስለዚህም እውነትን ለማግኘት ብለው አይመረምሩም። ዳዊት እንዳለው ልባቸው እንደወተት ረካ። ከአባቶቻቸው በሰሙት ልባቸው ረክቷል። እውነት ወይም ሐሰት ሊሆን ይችላል ብለው አልመረመሩም። እኔም ጌታ ሆይ ፍርድህን እንዳውቅ ያሳመንከኝ ይገባኛል አልኩ። አንተ በእውነት ቀጣኸኝ፣ በምህረትህም ገስፀኸኝ። አንተ አዋቂ አድርገህ የፈጠርከኝ ጥበበኛ አድርገኝ እንጂ የዋሾ መምህራንና የሐጢአትን ቅብአት እራሴን አልቀባም። እኔ አዋቂ ብሆን ምን አውቃለሁ ብዬ አሰብኩ። ከፍጥረት ሁሉ የሚልቅ ፈጣሪ እንዳለ አውቃለሁ። ከታላቅነቱ የተረፈ ታላላቅን ፈጥሯልና። ሁሉንም የሚያውቅ ነው። ከአዋቂነቱ በተረፈ አዋቂዎች አድርጎ ፈጥሮናልና። ለርሱ ልንሰግድለት ይገባል። እርሱ የሁሉ ጌታና ሁሉንም የያዘ ነውና ወደ እርሱ በፀለይን ጊዜ ይሰማናል። እግዚአብሔር አዋቂ አድርጎ የፈጠረን በከንቱ አይደለም። እንዲህ አድርጎ የፈጠረኝ እንድፈልገውና እርሱ በጥበቡ በፈጠረኝ መንገድ እንዳውቀው እስካለሁም ድረስ እንዳመሰግነው ነው ብዬ አሰብኩ። ሰዎች ሁሉ ሐሰት ካልሆነ በስተቀር ስለምን እውነት አይናገሩም ብዬ አሰብኩ። የሰው ፍጥረት ታካችና ደካማ መሰለኝ። ሰው ግን ጽድቅን ቢወዳትና በጣም ቢያፈቅራት የተሸሸገውንም ፍጥረትን ቢያውቅ ይወዳል። ይህም ነገር እጅግ ጥልቅ ነውና በትልቅ ድካምና ትዕግሥት ካልሆነ በስተቀር አይገኝም። ጠቢቡ ሰለሞን

"ከፀሐይ በታች ስለተደረገው ሁሉ ጥበብን ለመፈለግና ለመመርመር ልቤን ሰጠሁ። እግዚአብሔር ለሰው ልጆች እንዲደክሙበት የሰጣቸውን ክፉ ስራ አየሁ" ይላል። ስለዚህም ሰዎች ሊመረምሩ አይፈልጉም። ሳይመረምሩ ከአባቶቻቸው የሰሙትን ማመን ይመርጣሉ። ነገር ግን እግዚአብሔር ሰውን የምግባሩ ጌታ ክፉ ወይም መልካም የፈለገውን እንዲሆን ፈጠረው። ሰውም ክፉና ዋሾ መሆንን ቢመርጥ ለክፋቱ የሚገባውን ቅጣት እስኪያገኝ ድረስ ይቻላል። ነገር ግን ሰው ስጋዊ ነውና ለስጋው የሚመቸውን ይወዳል። ክፉ ይሁን መልካም ለስጋው ፍላጎት የሚያገኝበትን መንገድ ሁሉ ይፈልጋል። እግዚአብሔር ሰው የፈለገውን እንዲሆን ለመምረጥ መብት ሰጠው እንጂ ለክፋት አልፈጠረውም። ስለዚህ መምረጥ ክፉ ቢሆን ለቅጣት መልካም ቢሆን ደግሞ የመልካምነት ዋጋ ለመቀበል የተዘጋጀ እንዲሆን እድል ሰጠው። በህዝብ ዘንድ ክብርና ገንዘብ ለማግኘት የሚፈልግ ዋሾ ሰው ነው። ዋሾ ሰው ይህን በሐሰተኛ መንገድ ሲያገኝ እውነት አስመስሎ ሀሰት ይናገራል። ሊመረምሩ የማይፈልጉ ሰዎች እውነት ይመስላቸውና በእርሱ በፅኑ ሃይማኖት ያምናሉ። እስኪ ሕዝባችን በስንት ውሸት ያምናል? በጽኑ ሃይማኖት ያምናል። በሀሳብ ከዋክብትና በሌላም አስማት፤ አጋንንት በመሳብና በመርጨት፣ አስማት በማድረግ፣ በጥንቆላ ሁሉ ያምናሉ። ይህን ሁሉ መርምረው እውነቱን አግኝተው አያምኑም። ነገር ግን ከአባቶቻቸው ሰምተው ያምናሉ። እነዚያስ የፈተኞቹ ገንዘብና ክብር ለማግኘት ካልሆነ በቀር ስለምን ዋሹ? እንዲሁ ህዝብን ሊገዙ

የሚፈልጉ ሁሉ እውነት እንነግራችኋለን እግዚአብሔር ወደ እናንተ ላከን ይሏቸዋል፡፡ ህዝቡንም ያምናሉ፡፡ ከነርሱም በኋላ የመጡት እነሱ ሳይመረምሩ የተቀበሏትን ያባቶቻቸውን እምነት አልመረመሩም፡፡ ከዛ ይልቅ ለእውነት ለሃይማኖታቸው ማስረጃ ታሪክን፣ ምልክቶችን፣ ተዓምራትን እየጨመሩ አፀኑት፡፡ እግዚአብሔርንም የሐሰተኞች ተካፋይና የሐሰት ምስክር አደረጉት፡፡

## ጥልቅ ምርመራ ስለ ሙሴና መሐመድ ሕግጋት

ለሚመረምር ግን እውነት ቶሎ ይገለፃል፡፡ ፈጣሪ በሰው ልብ ያስገባውን ንፁህ ልቦና የፍጥረት ሕግጋትና ስርዓትን ተመልክቶ የሚመረምር እርሱ እውነትን ያገኛል፡፡ ሙሴ ፈቃዱንና ሕጉን ልነግራችሁ ከእግዚአብሔር ዘንድ ተልኬ መጣሁ ይላል፡፡ ከርሱ በኋላ የመጡት በግብፅና በደብረሲና እንዲህ ተደረገ እያሉ ታሪክን፣ ተዓምራትን እየጨመሩ የሙሴን ነገር እውነት አስመሰሉት፡፡ የሙሴ መጽሐፍ ከፍጥረት ሕግ ስርዓትና ከፈጣሪ ጥበብ ጋር አይስማማም፡፡ በውስጡ የተሳሳተ ጥበብ ይገኛል፡፡ ለሚመረምር ግን እውነት አይመስለውም፡፡ በፈጣሪ ፍቃድና በፍጥረት ህግ የሰው ልጅ እንዳይጠፋ ልጆችን ለመውለድ ወንድና ሴት በፍትወተ ስጋ እንዲገናኙ ታዟል፡፡ ይህም ግንኙነት እግዚአብሔር ለሰው በሕገ ተፈጥሮው የሰጠው ነው፡፡ እግዚአብሔር የእጁን ስራ አያረክስም፡፡ እግዚአብሔር

ዘንድ እርኩሰት ሊገኝ አይችልም። ሙሴ ይህን ማለቱ ትክክል ነው አልልም። ፈጣሪውን ዋሾ እንዳደረገው ልቦናችን ያስረዳናል። እንደገናም የክርስቲያን ህግ ለማስረጃዋ ተአምራቶች ተገኝተዋልና ከእግዚአብሔር ናት ይላሉ። ነገር ግን የወሲብ ስርዓት የተፈጥሮ ስርዓት እንደሆነ ምንኩስና ግን ልጆች ከመውለድ ከልክሎ የሰውን ፍጥረት አጥፍቶ የፈጣሪን ጥበብ የሚያጠፋ እንደሆነ ልቡናችን ይነግረናል ያስረዳናል። የክርስቲያን ሕግ ምንኩስና ከወሲብ ይበልጣል ብትል ሐሰት ትናገራለችና ከእግዚአብሔር አይደለችም። የፈጣሪን ህግ የሚያፈርሰው እንዴት ከጥበቡ በለጠ? ወይስ የእግዚአብሔርን ሥራ የሰው ምስክር ሊያስተካክለው ይቻለዋልን?

እንዲሁ መሐመድ የማዛችሁ ከእግዚአብሔር የተቀበልኩትን ነው ይላል። መሐመድን መቀበል የሚያስረዱ ተዓምራት ፀሐፊዎች አልጠፉምና በሱም አመኑ። እኛ ግን የመሐመድ ትምህርት ከእግዚአብሔር ሊሆን እንደማይችል እናውቃለን። የሚወለዱ ሰዎች ወንድና ሴት ቁጥራቸው ትክክል ነው። በአንድ ሰፊ ቦታ የሚኖሩ ወንድ ሴት ብንቆጥር ለእያንዳንዱ ወንድ አንዲት ሴት ትገኛለች እንጂ ለአንድ ወንድ ስምንት ወይም አስር ሴቶች አይገኙም። የተፈጥሮ ህግም አንዱ ከአንዲት ጋር እንዲጋቡ አዟል። አንድ ወንድ አስር ሴት ቢያገባ ግን ዘጠኝ ወንዶች ሴት የሌላቸው ይቀራሉ። ይኸም የፈጣሪን ስርዓትና ሕገ ተፈጥሮን የጋብቻንም ጥቅም ያጠፋል። አንድ ወንድ ብዙ ሴቶች ሊያገባ ይገባዋል ብሎ በእግዚአብሔር ስም ያስተማረ መሐመድ

ግን ትክክል ነው አልልም:: ከእግዚአብሔር ዘንድ አልተላከም:: ጥቂት ስለ ጋብቻ ሕግ መረመርኩ:: የቀረውን ብመረምርም በሕገ ኦሪትና በክርስትና በእስልምና ህግ ፈጣሪ በልቡናችን ከሚገልጽልን እውነትና እምነት ጋር አይስማማም:: ብዙ አይገኝበትም አልኩ:: ፈጣሪ ለሰው ልጅ ክፉና መልካም የሚለይበት ልቦና ሰጥቶታል:: በብርሀን ብርሀን እናያለን እንደተባለውም የሚገባውን የማይገባውን ሲያውቅ፣ እውነትን ከሀሰት እንዲለይ ነው:: ስለዚህም የልቦናችን ብርሀን እንደሚገባ በእርሱ ብናይበት ሊታይልን አይችልም:: ፈጣሪያችን ይሄን ብርሃን የሰጠን በርሱ እንድንድን ነው እንጂ እንድንጠፋ አይደለም:: የልቦናችን ብርሀን የሚያሳየን ሁሉም ከእውነት ምንጭ ነው:: ሰዎች ከሐሰት ምንጭ ነው ቢሉን ግን ሁሉን የሰራ ፈጣሪ ቅን እንደሆነ ልቦናችን ያስረዳናል:: ፈጣሪ በመልካም ጥበቡ ከሴት ልጅ ማህፀን በየወሩ ደም እንዲፈስ አዟል:: ሙሴና ክርስቲያኖች ግን ይህን የፈጣሪ ጥበብ እርኩስ አደረጉ:: እንደገና ሙሴ እንዲህ ያለችውን ሴት የተገናኛትን ያረክሳል:: ይህም የሙሴ ህግ የሴትን ኑሮ በሙሉና ጋብቻዋን ከባድ አድርጎታል:: የመራባትንም ህግ አጥፍቷል:: ልጆችን ከማሳደግ ከልክሎ ፍቅርንም ያፈርሳል:: ስለዚህም ይህ የሙሴ ህግ ሴትን ከፈጠረ ሊሆን አይችልም:: እንደገናም የሞቱትን ወንድሞቻችንን ልንቀብራቸው ተገቢ መሆኑን ልቦናችን ይነግረናል:: በድኖቻቸውም በሙሴ ጥበብ ካልሆነ በስተቀር ከመሬት የተፈጠርንበት ወደ መሬትም ልንገባ ባዘዘን በፈጣሪያችን ጥበብ እርኩሳን አይደሉም:: ነገር ግን ለፍጥረት ሁሉ

እንደማይገባ በትልቅ ጥበብ የሰራ እግዚአብሔር ስርዓቱን አያረክሰውም። ሰው ግን የሀሰትን ቃል እንዳያከብር ብሎ ሊያረክሰው ይፈልጋል። እንደገና ወንጌል አባትና እናቱን ምሽቱንና ልጁን ያልተወ ለእግዚአብሔር የተገባ አይሆንም ይላል። ይህ መተው የሰውን ፍጥረት ሁሉ ያጠፋል። እግዚአብሔር ግን ፈጥረቱን በማጥፋት አይደሰትም። አባትና እናትም በሽምግልናቸው ጊዜ እረዳት አጥተው እንዲሞቱ መተው ትልቅ አበሳ መሆኑን ልቦናችን ያሳየናል። እግዚአብሔርም አመጻን የሚወድ አምላክ አይደለም። ልጆችን መተው ግን ከበረሃ አራዊት ይብሳሉ። ምሽቱ ስታመነዝር የሚፈታት ሁሉ የፈጣሪን ስርዓትና የተፈጥሮን ህግ አፍርሷል። ስለዚህ ወንጌል በዚህ ስፍራ የሚለው ከእግዚአብሔር ሊሆን አይችልም። እንደገና በእስልምና ሰው እንደ እንስሳ ሊሸጥና ሊገዛ ይገባል ይላሉ። ፈጣሪያችን እንደ ወንድሞች አስተካክሎ ከፈጠረን ከሰዎች ፈጣሪ ይህ የእስልምና ህግ ሊወጣ አይችልም። ልቦናችን ያውቃል እነሱ ግን ደካማን ሰው የሐይለኛ ሰው ንብረት አደረጉት። አዋቂው ፍጥረትንም ካላዋቂ እንስሳ ጋር አስተካከሉት ይህ ከእግዚአብሔር ዘንድ ሊወጣ ይችላልን? እንደዚሁም እግዚአብሔር የከንቱን ነገር አያዝም። ይህን ብላ፣ ይህን አትብላ፣ ዛሬ ብላ፣ ነገ አትብላ አይልም። ለክርስቲያኖች እንደሚመስላቸውና የጾም ሕግጋት እንደሚጠብቁ ስጋን ዛሬ ብላ ነገ ግን አትብላ አይልም። እስላሞችንም እግዚአብሔር ሌሊት ብሉ ቀን አትብሉ ብሎ ይሄንና የመሳሰሉትን አይላቸውም። የፍጥረታችን ጤና የማያውክ ነገር ሁሉ

ልንበላ እንደሰለጠንን ልቦናችን ያስተምረናል። አንድ የመብል ቀን አንድ የፆም ግን ጤናን ያውካል። የፆም ህግ መብላትን ለሰው ሕይወት ከፈጠረና ልንበላቸው ከፈቀደ ፈጣሪ የወጣ አይደለም። በልተን ልናመሰግነው እንጂ በረከቱን ልናርም አይገባንም። ሕገ ፆም የስጋን ፍትወት ለመግደል የተሰራ ነው የሚሉም ቢኖሩ ፍትወተ ስጋ ወንድ ወደ ሴት ሲሳብ ሴትም ወደ ወንድ ልትሳብ የፈጣሪ ጥበብ ነውና እርሱ ፈጣሪ በሰራው በታወቀ በስጋዊ መገናኘት ስርዓት ካልሆነ በስተቀር ማጥፋት አይገባም እላለሁ።

ፈጣሪያችን ይህን ፍትወት ለሰው ለእንስሳት ሁሉ በከንቱ አልሰጠም። ነገር ግን ለዚህ አለም ሕይወትና ፍጥረት የተሰራለት መንገድ ሁሉ መሠረቱ ሆኖ እንዲቆይ ይህ ፍትወት ለሰው ልጅ ተሰጠ። አስፈላጊያችንን ልንበላ ይገባናል። በእሁድ ቀንና በበዓል ቀናት በአስፈላጊው ልክ የበላ እንዳልበደለ እንዲሁ በአርብ ቀንና ከፋሲካ በፊት ባሉት ቀናት ለክቶ የሚበላ አልበደለም። እግዚአብሔር ሰውን በሁሉ ቀንና በሁሉ ወራት ካስፈላጊ ምግብ ጋር አስተካክሎ ፈጥሮታል። አይሁድ፣ ክርስቲያንና እስላም ግን የፆምን ህግ ባወጡ ጊዜ ይህን የእግዚአብሔር ስራ ልብ አላሉም። እግዚአብሔር ጾምን ሰራልን እንዳንበላም ከለከለን እያሉ ይዋሻሉ። እግዚአብሔር ፈጣሪያችን ነው። ግን የምንበላውን ምግባችንን እንድንመገበው ሰጠን እንጂ እርሱን ልናርም አይደለም።

## ስለ ሐይማኖቶች መለያየት

ሌላ ትልቅ ምርመራ አለ። ሰዎች ሁሉ በእግዚአብሔር ዘንድ ትክክል ናቸው። ሁሉ ፍጥረቶች አዋቂዎች ናቸው። እሱም አንድ ህዝብ ለህይወት አንድ ሕዝብ ለሞት አንድም ህዝብ ለምህረት አንድም ለኩነኔ አልፈጠረም። ይህም አድሎ በስራው ሁሉ ፃድቅ በሆነ በእግዚአብሔር ዘንድ እንደማይገኝ ልቦናችን ያስተምረናል። ሙሴ ግን አይሁድን ለብቻቸው እንዲያስተምራቸው ተላከ። ለሌሎች ሕዝቦች ፍርዱ አልተነገረም። እግዚአብሔር ስለምን ለአንድ ሕዝብ ፍርድ ሲነግር ለሌላው አልነገረም። በዚህም ጊዜ ክርስቲያኖች የእግዚአብሔር ትምህርት ከእኛ ጋ ካልሆነ በስተቀር አይገኝም ይላሉ። አይሁድና እስላም የህንድ ሰዎችም ሌሎችም ሁሉ እንደነሱ ይላሉ። እንዲሁ ደግሞ ክርስቲያኖች እርስ በርሳቸው አይስማሙም። ካቶሊኮች እግዚአብሔር ከኛ ጋር ነው ያለ እንጂ ከናንተ ጋ አይደለም ይሉናል። እኛም እንዲሁ እንላለን። ሰዎች እንደምንሰማቸው ግን የእግዚአብሔር ትምህርት እጅግ ጥቂቶች ወደ ሆኑት እንጂ ለብዙዎቹ አልደረሰም። ከእነዚህ ሁሉ ደግሞ ወደ ማን እንደደረሰ አናውቅም። እግዚአብሔር ከፈቀደ ቃሉን በሰው ዘንድ ማፅናት ተስኖት ነውን? ሆኖም ግን የእግዚአብሔር ጥበብ በመልካም ምክር ይህ ነገር እውነት እንዳይመስላቸው ሰዎች በሀሰት ሊስማሙ አልተወም። ሰዎች ሁሉ በአንድ ነገር በተስማሙ ጊዜ ይህ ነገር እውነት ይመስላል።

ሰዎች ሁሉ በሃይማኖታቸው ምንም እንደማይስማሙ በሃሳብም ሊስማሙ አይችሉም:: እስኪ እናስብ ሰዎች ሁሉ ሁሉን የፈጠረ እግዚአብሔር አለ በማለታቸው ስለምን ይስማማሉ? ፍጡር አለ ፈጣሪ እንደማይችል፣ ስለዚህ ፈጣሪ እንዳለ እውነት ሲገኝ ነው:: ይህ የምናየው ሁሉ ፍጡር እንደሆነ የሰው ሁሉ ልቦና ያውቃል:: ሰዎች ሁሉ በዚህ ይስማማሉ:: ነገር ግን ሰዎች የሚያስተምሩትን ሃይማኖት በመረመርን ጊዜ በውስጡ ሐሰት ከእውነት ጋር ተቀላቅሎበታል:: ስለዚህ እርስ በርሱ አይስማማም:: ሰዎች እርስ በርሳቸው አንዱ ይህ እውነት ነው ሲል:: ሁለተኛው አይደለም ሀሰት ነው ሲል ይጣላሉ:: ሁሉም የእግዚአብሔርን ቃል የሰው ቃል እያደረጉ ይዋሻሉ:: እንደገናም የሰው ሀይማኖት ከእግዚአብሔር ብትሆን ክፉዎችን ክፉ እንዳያደርጉ እያስፈራራች መልካም እንዲያደርጉ ትፈቅድላቸው ነበር:: ደጎችንም በትዕግስታቸው ታፀናቸው ነበር:: ለኔም እንዲህ ያለው ሃይማኖት ባሏ ሳያውቅ በምንዝርና የወለደች ሴትን ትመስለኛለች:: ባሏ ግን ልጁ ስለመሰለው በሕፃኑ ይደሰታል:: እናቲቱንም ይወዳታል:: በዝሙት እንደወለደችው ባወቀ ጊዜ ግን ያዝናል:: ሚስቱንም ልጅዋንም ያባርራል:: እንዲሁም እኔም ሀይማኖቴን አመንዝራና ዋሾ መሆኑዋን ካወኩ በኋላ ስለርሷ በዝሙት ስለተወለዱ ልጆቿ አዘንኩ:: እነሱ በጠብ፣ በማሳደድ፣ በመማታት፣ በማሰር፣ በመግደል ወደዚህ ዋሻ ያባረሩኝ ናቸው:: ነገር ግን የክርስቲያን ሃይማኖት እውነት ናት እንዳልል በዘመነ ወንጌል እንደተሰራ ክፉ አልሆነችም:: የምህረትን ስራ በሙሉ እርስ በርስ

መፋቀርን ታዛለች። በዚህ ዘመን ግን የሃገራችን ሰዎች የወንጌልን ፍቅር ወደ ጠብና ሃይል ወደ ምድራዊ መርዝ ለወጡት። ሃይማኖታቸውን ከመሰረቱ አመጻ እየሰሩ ከንቱ ያስተምራሉ። በሀሰትም ክርስቲያኖች ይባላሉ።

## ስለ አምላክ ሕግና ስለ ሰው ሕግ

እግዚአብሔር የገዛ ሕዝቡን እንዲያስቷቸው ስለምን ዋሾ ሰዎችን ይተዋል ብዬ አሰብኩ። እግዚአብሔር ግን ለሁሉም ለእያንዳንዱ እውነትንና ሀሰትን እንዲያውቅ ልቦና ሰጥቶናል። እውነት ወይም ሀስት እንደፈቃዱ የሚመርጥበት መምረጫ ሰጠው። እውነትን ብንወድ ለፍጥረት ሁሉ አስፈላጊና ተገቢ የሆነውን እርሱም እንድናይበት እግዚአብሔር በሰጠን ልቦናችን ውስጥ እንፈልጋት። ሰው ሁሉ ዋሾ ነውና እውነትንም በሰዎች ትምህርት አታገኟትም። ከእውነት ይልቅ ሀሰትን ብንመርጥ ስለዚህ እኛ በስህተታችን እንጠፋለን እንጂ ለፍጥረት ሁሉ የተሰራው የፈጣሪ ስርዓትና ህግ አይጠፋም። እግዚአብሔር ማንንም በሰራው ሥራ ይጠብቀዋል። ከሰው ስራ ግን የእግዚአብሔር ስራ ይፀናል። የሰው ስራ ሊያጠፋው አይችልም ስለዚህም ከጋብቻ ይልቅ ምንኩስናን ይበልጣል ብለው የሚያምኑ እነርሱ በፈጣሪ ስራ ፅናት ወደ ጋብቻ ይሳባሉ። ጾም ነፍስ እንደሚያፀድቅ የሚያምኑ እነርሱ ደግሞ እረሃብ በበዛባቸው ጊዜ ይበላሉ። ገንዘቡን የተወ ፍፁም እንዲሆን የማያምኑ በገንዘብ ለሚያገኙት ጥቅም ወደ ገንዘብ መፈለግ ይሳባሉ። ብዙዎች የሀገራችን መነኩሴዎችም እንደሚያደርጉት ከተውት በኋላ እንደገና

ይፈልጉታል። እንደዚሁ ቀሸዎች ሁላቸው የተፈጥሮን ስራ ሊያፈርሱት ይፈልጋሉ። ነገር ግን ደካማነታቸውን ያሳያሉ እንጂ አይችሉም። ፈጣሪም ይስቅባቸዋል። የፍጥረት ጌታም በላያቸው ይሳለቅባቸዋል። እግዚአብሔር የእግዚአብሔርን ፍርድ ማድረግ ያውቃልና ሀጥአንም በእጁ ስራ ወጥመድ ተጠመደ። ስለዚህም የጋብቻን ሥርዓት የሚያስነውር መነኩሴ በክፉ በሽታና ፍጥረቱ ባልሆነ በሌላ የሴት አበሳ በዝሙት ተፅኖ ስር ይጠመዳል። ገንዘባቸውን የሚንቁ ገንዘብ እንዲያገኙ በሀብታሞችና በነገሥታት ዘንድ ግብዞች ይሆናሉ። ለእግዚአብሔር ብለው ዘመዶቻቸውንም በሽምግልናቸው በችግራቸው እረዳት ባጡ ጊዜ የተው በነሱ ሽምግልና ጊዜ ሰውና እግዚአብሔርን ወደ ማማት መሳደብ ይደርሳሉ። እንደዚሁም የፈጣሪን ስርዓት የሚያፈርሱ ሁሉ በእጃቸው በሰሩት ወጥመድ ይወድቃሉ። እንደገናም እግዚአብሔር ክፉትን ስህተትን በሰው መካከል ይተዋል። ነፍሶቻችን በዚህ ዓለም የእግዚአብሔር ጥበብ የፈጠረውን የፈተና ቀን ይኖራሉ። ጠቢቡ ሰለሞን "እግዚአብሔር ፃድቃንን ፈተናቸው። ወርቅ በእሳት እንደሚፈተን ይፈትናቸዋል። ለእርሱ የተዘጋጁ ሆነውም አግኝቷቸዋልና። እንደተወደደ ዕጣን መአዛም ይቀበላቸዋል" ይላል።

ከሞታችን በኋላም ቢሆን ወደ ፈጣሪያችን በገባን ጊዜ እግዚአብሔር በእውነትና በትልቅ በጥበብ የሰራው ሁሉ እውነትና ቅን የሆነውን መንገድ ሁሉ እንለያለን። ነፍሳችንም ከስጋዊ ሞታችን በኋላ እንደምንሄድ ይታወቃል። በዚህ ዓለም ውዴታችን አይፈፀምምና

የሌላቸው ይፈልጋሉ ያላቸው ባላቸው ላይ እንደገና ሊጨምሩ ይፈልጋሉ። ሰው በዚህ ዓለም ያለው ሁሉ እንኳን ቢኖረው እንደገና ይወዳል እንጂ አይጠግብም። ይህም የፍጥረታችን ጠባይ ለሚመጣው ኑብረት እንጂ ለዚህ ዓለም ኑብረት ብቻ እንዳልተፈጠርን ያመለክታል። በዚያውም የፈጣሪያቸውን ፈቃድ የፈፀሙ ነፍሳት ፍፁም ይጠግባሉ እንጂ ከእንግዲህ ሌላ አይወዱም። አለዚያ ግን የሰው ፍጥረት አስፈላጊውን ሁሉ አላገኘምና ጎዶሎ በሆነ ነበር። እንደገናም ነፍሳችን እግዚአብሔርን ማሰብ ትችላለችና በሀሳቧም ታየዋለች። እንደገናም ለዘላለም መኖር ማሰብ ትችላለች። እግዚአብሔርም ይህን ማሰብ በከንቱ አልሰጣትም። ነገር ግን እንደሰጣት ልታስብና እንድታገኝም ሰጣት። ደግሞ በዚህ ዓለም ፅድቅ ሁሉ አይፈፀምም። ክፉ ሰዎች ከዚህ ዓለም መልካም ይጠግባሉ። ደጋጎች ይራባሉ። እሚደሰት ክፉ አለ፤እሚያዝን ደግ አለ፤እሚደሰት አመፀኛ አለ፤ እሚያለቅስ ፃድቅም አለ፤ስለዚህ ከሞታችን በኋላ ለሁሉ እንደየምግባሩ እሚከፈለው ሌላ ኑሮና ፍፁም ፅድቅ ያስፈልጋል። በብርሀን ልቦናቸው ተገለፀላቸው። የፈጣሪን ፈቃድ የፈፀሙና በተፈጥሯቸውም ፀባያዊ ሕጉን የጠበቁ ዋጋቸው ይከፈላቸዋል። የተፈጥሮን ሕግ ከመረመርን የተረጋገጠ መሆኑን ልቦናችን በግልፅ ይነግረናል። ነገር ግን ሰዎች ሊመረምሩ አልፈለጉምና የፈጣሪያቸውን ፈቃድ በእውነት ከመፈለግ የሰዎችን ቃል ማመን መረጡ።

## <u>ስለ ባህሪያዊ ዕውቀት</u>

የፈጣሪ ፈቃድ ግን ለእግዚአብሔር ለፈጣሪህ ስገድ፣ ሰውንም ሁሉ እንደ ነፍስህ አፍቅር ይላል። ይህ በልቦናችን እውነት መሆኑ ይታወቃል። እንደገናም በልቦናችን እውነትነቱ የሚታወቅ ሌላ እውነት "ሊያደርጉብህ የማትፈልገውን በሰው አታድርግ። ላንተ ሊያደርጉልህ የምትፈልገውን አድርግላቸው" ይላል። የሰንበትን ማክበር የሚለው ካልሆነ በቀር አሥሩ የኦሪት ትዕዛዛት የፈጣሪ ናቸው። ሰንበትን ስለማክበር ግን ልቦናችን ዝም ይላል። ልንገድልና ልንሰርቅ፣ ልንዋሽና የሰው ሚስት ልንሰርቅ ይህን የሚመስለውን ልናደርግ እንደማይገባን ልቦናችን ይነግረናል። እንዲሁም ስድስቱ የወንጌል ቃላት የፈጣሪ ፈቃዶች ናቸው። እኛ ይህን የምህረት ስራ ሊያደርጉልን እንፈልጋለን። በሚቻለን ለሌሎች ልናደርግላቸው ይገባናል። ደግሞም በዚህ ዓለም ህይወታችን፣ ንብረታችን እንድጠብቅ የፈጣሪ ፈቃድ ነው። ከፈጣሪ ፈቃድ ወጥተን በዚህ ህይወት እንኖራለን። በተቀደሰ ፈቃዱ ካልሆነ በቀር ልንተወው አይገባንም። እርሱ ፈጣሪያችን ለሁሉ ልቦናና ችሎታ ስለሰጠ ኑሮአችንን በእውቀትና በስራ እንድናሳምረው ይፈቅድልናል። ይህ ካልሆነ በቀር የሕይወታችን ፍላጎት አይገኝም። እንዲሁ ከአንዷ ጋር መጋባትና ልጆች ማሳደግን ፈቅዷል። ደግሞም ከልቦናችን ጋር የሚስማማ ለህይወታችንም ለሁሉም የሰው ልጆች ኑሮ የሚያስፈልጉ ሌሎች ብዙ ስራዎች አሉና የፈጣሪ ፈቃድም እንዲሁ ስለሆነ ልንጠብቀው ይገባናል። እግዚአብሔር ፍፁማን አድርጎ እንዳልፈጠረን ልናውቅ ይገባናል። ለመፈፀማችን የተዘጋጀን አዋቂዎችና

በዚህም ዓለም እስካለን ድረስ እንድንፈፀም ፈጣሪያችን በጥበቡ ላዘጋጀልን ዋጋ የተዘጋጀን እንድንሆን አድርጎ ፈጠረን። በዚህ ምድር ፍፁማንና ብፁአን አድረጎ ሊፈጥረን ለእግዚአብሔር ይቻለው ነበር። ነገር ግን ለመፈፀማችን እምንዘጋጅ አድርጎ ፈጠረን እንጂ እንዲሁ ሊፈጥረን አልፈቀደም። ከሞታችን በኋላ ፈጣሪያችን ለሚሰጠን ዋጋ የተዘጋጀን ፍጹማን እንድንሆን በዚህ የፈተና ዓለም መካከል አኖረን። በዚህ ዓለም እስካለንም ወደ እርሱ እስኪወስደን ድረስ እየታገስንና ፈቃዱን እየፈፀምን ፈጣሪያችንን ልናመሰግነው ይገባል። የፈተናችንንም ጊዜያቶች እንዲያቀልልን ባለማወቃችን የሰራነውን የዕብደት አበሳ እንዲተውልን የተፈጥሮ ሕግጋትን አውቀን እንድንጠብቃቸው ልቦና እንዲሰጠን ወደ ቸርነቱ እንለምን። ፀሎት ደግሞ ላዋቂ ነፍስ አስፈላጊ ነውና ዘወትር ልንፀልይ ይገባናል። አዋቂ ነፍስ ሁሉን የሚያውቅና ሁሉን የሚጠብቅ ሁሉንም የሚገዛ እግዚአብሔር እንዳለ ታውቃለች። ወደ እርሱ እንድትፀልይም ከእርሱ መልካም እንድትለምን፣ ከክፉ እንድትድንና ሁሉን ወደሚችል እጅ እንድትማፀን ወደ እርሱ ትሳባለች። እግዚአብሔር ምሁርና ትልቅ ነው። የሚሳነው የለም። ከበታቹ ያለውን ያያል፣ ሁሉንም ይይዛል፤ ሁሉን ያውቃል፣ ሁሉን ይመራል፣ሁሉን ያስተምራል አባታችን ፈጣሪያችን፣ ጠባቂያችን ነው። የነፍሳችን ዋጋ ቸርና ይቅር ባይ ችግራችንን ሁሉ የሚያውቅ ነው። ለሕይወት እንጂ ለጥፋት አልፈጠረንም። በትዕግስታችንም ይደሰታል። ጠቢቡ ሰለሞን

"ጌታ ሆይ አንተ ከሁሉ በላይና ቻይ ነህና ሁሉን ታስተምራለህ፣ሰዎችንም ለንስሐ ታቆያቸዋለህ፣ሐጢያታቸውንም ችላ ትላለህ፣ አንተም ያደረከውን ሁሉ ምንም የምትንቀው ስለማይኖር ሁሉን ትወዳለህ። በሁሉ ፍጥረት ላይም ትራራለህና ይቅር ትላለህ" ይላል። የእግዚአብሔርም ታላቅነቱን እንድናስብ ለስጋችንና ለነፍሳችን እሚያስፈልገንን ለማግኘት ወደ እርሱ እንድንፀልይና እንድናመሰግነው አዋቂዎች አድርጎ ፈጠረን። ይህን ሁሉ በሰው ልብ ያገባ ፈጣሪያችን እውቀት ያስተምራልና እንዴትስ ሐሰት ሊሆን ይችላል።

## ስለ ፈተናና ፀሎት

እኔም እንደገና በሙሉ ልባችን በፍቅርና በእምነት በትዕግስትም ወደ እርሱ በፀለይን ጊዜ እግዚአብሔርም ፀሎታችንን እንደሚሰማ በሌላ መንገድ አወኩ። እኔ በልጅነት ጊዜዬ ስለ እግዚአብሔር ስራ ምንም ሳላስብ ወደ እርሱ ስፀልይ ሐጢአተኛ ነበርኩ። ለአዋቂ ፍጥረት የማይገባ ብዙ በደልኩ። ስለሐጢአቴም ሰው ከእርሱ ሊያመልጥ ወደማይችለው ወጥመድ ወደኩ። ፈፅሜ ልጠፋም ቀረብኩ። የሞት ፍርሃትም መጣብኝ። የዚያን ጊዜ ወደ እግዚአብሔር ተመልሼ እርሱ የማዳንን መንገድ ያውቃልና እንዲያድነኝ ብዬ ወደ እርሱ መፀለይ ጀመርኩ። እግዚአብሔርንም ጌታ ሆይ በሐጢአቴም እፀፀታለሁ ፈቃድህንም ለማድረግ እፈልጋለሁ አልኩ። በሙሉ ልቤም ብዙ ጊዜ ፀለይኩ። እግዚአብሔርም ሰማኝና ፈፅሞ አዳነኝ። ወደ እርሱ ተመልሼ በፍፁም ልቤ አመሰገንኩት። በመዝሙረ ዳዊት "እግዚአብሄር

የልመናዬን ቃል ስምቷልና ወደድኩት" የሚለውንም ዘመርኩ። ደገምኩት። ይህም መዝሙር ስለእኔ የተፃፈ መሰለኝ። እንደገናም ልድን ካልሆነ በስተቀር አልሞትም። የእግዚአብሔርንም ስራ እነግራለሁ አልኩ። ነገር ግን ዘወትር ወደ ንጉሥ የሚያሳጡኝን ነበሩ። ይህ ሰው ጠላትህ ነው፣ ለፈረንጆቹም ጠላታቸው ነው ይሉታል። የንጉሡም ቁጣ በላዬ እንደተቃጠለ አወኩ። አንድ ቀንም የንጉሡ መላእክተኛ መጥቶ ንጉሱ ፈጥነህ ወደ እኔ ና ይልሃል አለኝ። እኔም እጅግ ፈራሁ። የንጉስ ሰዎች ስለሚጠብቁኝም ልሸሽ አልቻልኩም። ባዘነ ልቤም ሌሊት በሙሉ ፀለይኩ። ሲነጋም ተነስቼ ሄጄ ወደ ንጉሱ ገባሁ። እግዚአብሔርም የንጉሱን ልብ ስላራራው በፍቅር ተቀበለኝ። ስለፈራሁት ነገርም ምንም አላለኝ። ነገር ግን ስለትምህርትና የመፅሀፍት ነገር ጠየቀኝ። አንተ የተማርክ ሰው ነህ፣እነርሱም በጣም የተማሩ ናቸው። ፈረንጆቹን ትወዳቸው ዘንድ ይገባሀል አለኝ። ስለፈራሁትም እሺ ፈረንጆቹ በእውነት የተማሩ ናቸው አልኩት። ከዚህም በኋላ ንጉሱ አምስት ወቄት ወርቅ ሰጥቶ በሰላም ሰደደኝ። ከንጉሱ ወጥቼ እየተደነቅኩ ለኔ መልካም ስላደረገልኝ እግዚአብሔርን አመሰገንኩት። እንደገናም ወልደ ዮሐንስ ባሳጣኝ ጊዜ ልሸሸው ስለተቻለኝ እንደፊተኛው እንዲያድነኝ ሳልፀልይ ሸሸሁ። ሰው እግዚአብሔርን በከንቱ ሳይፈታተን የሚቻለውን ሁሉ ሊያደርግ ይገባል። አሁን ግን ስለሸሸሁና በዋሻዬም ስለሆንኩ፣ ቀድሞ ያላሰብኩትን እንዳስብና ለነፍሴም ትልቅ ደስታ እሚያስደስታት እውነትን እንዳወኩ፣ ወደ ፈጣሪዬ የመመለስ ፍፁምነት ምክንያት ስላገኘሁ

ፈጣሪዬን አመሰገንኩ። በእውነትም እግዚአብሔርን እንዲህ አልኩት። ፍርድህን እንዳውቅ ያሳመምከኝ ይገባኛል። ከመምህራን ጋር በነበርኩ ጊዜ ካስተዋልኩት ይልቅ ብቻዬን በዋሻዬ ሁኜ በጣም አስተውያለሁና። ይህም የገፍኩት እጅግ ትንሽ ነው። ይህን የመሳሰሉ ብዙ እያሰብኩ በዋሻዬ ቆየሁ። እግዚአብሔርም የፍጥረታቱን ምስጢር ለማወቅ ጥበብ ስለሰጠኝ አመሰገንኩት። ነፍሴም የእግዚአብሔርን ጥበብ ስራ ከማሰብ በቀር ሁሉን እየናቀች ወደ እርሱ ትሳብ ነበር። በሰፊው ልቤም በዳዊት መዝሙር ሁልጊዜ እፀልይ ነበር። ይህ ፀሎት በጣም ይጠቅመኛልና ሕሊናዬንም ወደ እግዚአብሔር ያነሳሳልኛል። በመዝሙረ ዳዊት ከሕሊናዬ ጋር የማይስማማ ባገኝሁ ጊዜ እኔ ተርጉሜ በእውቀቴ አስማማዋለሁ። ሁሉም ያምርልኝ ነበር። እንደዚህ እያልኩ በፀለይኩም ጊዜ በእግዚአብሔር መታመኔ ይጨምር ነበር። ሁልጊዜም እንደዚህ እል ነበረ።

"ጌታ ሆይ ፀሎቴን ስማኝ። ልመናዬንም ችላ አትበል። ከሰው ልጆች ግፊትም አድነኝ። ጌታ ሆይ ይቅርታህን ከኔ አታርቅ። ምህረትህም ፅድቅህም ዘወትር ያግኙኝ። ጌታ ሆይ ምኞቴን ሁልጊዜ እንድትሰጠኝም አልፈር። እንዲሁም እያልኩ ስምህን ለዘላለም እዘምራለሁ። ወደ እኔ ተመልከትና ይቅር በለኝ። ለባሪያህም ሀይል ስጠው። የደህንነት ምልክት ከእኔ ጋር አድርግና የባሪያህንም ልጅ አድነው። ስለስምህም ምራኝና መግበኝ። ነፍሴን ከሐጢያን ጋር አትሳባት። ምህረትህም ከበላዬ ትሁን። ባንተ ላይ ታምኛለሁና በንጋት እሚሰማ ምህረትን አድርግልኝ። በምድር ላይ ብፁእ አድርገህ ጠብቀኝ።

በጠላቶቹ እጅ አታግባኝ። ከተስፋዬ አታሳፍረኝ። ተድላ ደስታ አሰማኝ። እነርሱ ይረግማሉ አንተ ግን ባርከ። ይህም በጅህ እንደሆነ አወኩ።" ይህንንና የሚመስለውን በሙሉ በልቤ ቀንና ሌሊት እፀልይ ነበር። ስለፀሎት ስጋዊና መንፈሳዊ ስራ ጠዋትና ማታ የምጸልየው ጸሎትም እንዲህ ነበረ።

"ፈጣሪዬና ጠባቂዬ ሆይ እሰግድልሀለሁ በሙሉ ልቤም እወድሀለሁ ለሊትም ላደረክልኝ መልካምም አመሰግንሀለሁ። ሲነጋም በዚች ቀን ጠብቀኝ እልሀለሁ። ሲመሽም በዚችኛዋ ለሊት በዚችኛዋ ቀንና በህይወቴ ዘመን ሁሉ ፈቃድህን በእኔ ላይ እንዳውቀውና እንድፈጽመው አዋቂ አድርገኝ። ሐጢአቴንም ይቅር በለኝ። ለሕይወቴ የሚያስፈልገኝንም የሚበቃኝን ሁልጊዜ ስጠኝ። አንተን በመታመን ዘወትር አፅናኝ ጌታዬ ሆይ ስለቸርነትህና ስለሀይልህ ስለታላቅነትህም ከሰው ምላስና እጅ፣ከድህነት ከደዌ ስጋ፣ከነፍስ ሃዘንም አድነኝ።" ደግሞም በአንተ ታመንኩ የሚለውን በመዝሙር ያለውን እፀልይ ነበር። እንደገናም ፀሎት ብቻውን አይጠቅመኝምና ለህይወቴ የሚያስፈልገኝን በተቻለኝ ሁሉ ልሰራና ልደክም ይገባኛል ብዬ አሰብኩ። ነገር ግን ስራ አላውቅምና በእግዚአብሔር ሐይል እገባለሁ። ጌታ ሆይ ስራዬም አለበረከትህ ምንም አይጠቅመኝም። ሀሳቤን፣ኑሮዬን፣ ስራዬንም አንተ ባርከው። አንተ በምታውቀው በምትፈቅደው መንገድ ደስታንና ገንዘብ ስጠኝ። ከኔ ጋር በሥራ ያሉ ሰዎችን ልብ ወደ መልካም መልስልኝ። ሁሉ በተባረከው ፈቃድህ ይሆናልና ለኔም የሽምግልናዬን ጊዜ አሳምርልኝ። ልባችንም ዘወትር

በእግዚአብሔር እጅ እንደሆነ አወቅኩ፡፡ በበሽታና በድህነት በችግርም መካከል ብንኖር እግዚአብሔር ብፁአንና ደስተኞች ሊያደርገን ይችላል፡፡ እንደገናም በዚህ ዓለም በሀብትና በደስታ ሁሉ መካከል ብንኖር ጎስቋሎች ሊያደርገን ይችላል፡፡ ስለዚህ ድሆችና ችግረኞች በልባቸው ደስታ ሁልጊዜ ሲጫወቱ እናያለን፡፡ ሀብታሞችና ነገስታት በምኞታቸው ብዛት በሀብታቸው መካከል ሲያዝኑና ሲጎሳቆሉ እናያለን፡፡ እኛ ሳናውቀውና ሳንፈልገው የመነሻ ምክንያቱን ሳናውቅ ሐዘን በልባችን ውስጥ ይመጣል፡፡ በምድር ብፁአን እንዲያደርገንና ፍስሐና ደስታ እንዲሰማን ወደ እግዚአብሔር ልንፀልይ ይገባናል፡፡ እግዚአብሔር ለፃድቃን ብርሐን፣ ልባቸው ለቀና ደስታን ይሰጣቸዋል፡፡ እርሱ ያውቃልና የልባችንንም መንገድ ሁሉ ይገዛል፡፡ እርሱ በችግራችን ደስተኞች በድሎታችንም ሀዘንተኞች ሊያደርገን ይችላል፡፡ እግዚአብሔር እሚሰማን እንጂ ለሰዎች እንደሚመስላቸው በደስታና ሐዘን አይደርስንም፡፡ አንተ ፈጣሪዬና ጌታዬ በምድር እስካለሁ ድረስ ብፁዕ አድርገኝ ደስታና ትፍስህትንም አሰማኝ፡፡ ከሞቴ በኋላም ወደ አንተ ወስደህ ከአንተ አስጠጋኝ አልኩ፡፡ እንዲህ ብዬ ቀንና ማታ እየፀለይኩ ስነፍጥረትን፣እንስሳትን፣ የበረሃ አራዊትን በየሥርዓታቸው እያደነቅሁ ነበር፡፡ እነሱ ግን ሕይወታቸውን ለመጠበቅና ዘራቸውን ለማራባት በፀባየ ተፈጥሮአቸው ይሳባሉ፡፡ እንደገናም የበረሃ እንጨትና ሣር በትልቅ ጥበብ የተፈጠሩ ይበቅላሉ፣ ይለመልማሉ፣ ያብባሉ በየወገኖቻቸውም የዘራቸውን ፍሬ አለ ስህተት ያወጣሉና ነፍስ ያላቸውም ይመስላሉ፡፡ እንደገናም

ተራሮችና ኮረብቶች፣ ወንዞችና ውሃ ምንጮች ሥራ ሁሉ ስምህን ያመሰግነዋል። ጌታዬ ሆይ ስምህን በሁሉ በሰማይና በምድር እጅግ ተመስግኗል። ይህ የእጅህ ሥራ ፀሀይ የብርሃንና የዓለም ሕይወት ምንጭ እጅግ ትልቅ ነው። አንተ የሰራሃቸውን፣ የመሰረትካቸውን ጨረቃና ከዋክብትም አንተ ከሰራህላቸው መንገድ ሳይ አለመዛነፋቸው በጣም ያስደንቃል። ሌላ ደቃቃዎች የሚመስሉ ከዋክብትም በመራቃቸው እርቀታቸውን፣ ቁጥራቸውን፣ ታላቅነታቸውንስ የሚያውቅ ማነው? ደመናዎችም ልምላሜን ለማብቀል ውሀዎች ያፈሳሉ። ይህ ሁሉ ታላቅና እጅግ የሚያስደንቅ ጥበብ በጥበብ የተፈጠረ ነው። እንደዛም ብዬ እያደነኩና ፈጣሪዬን እያመሰገንኩ ሁለት ዓመት ተቀመጥኩ። እንደገናም የእግዚአብሔር ስራ እጅግ መልካም ነው። ሀሳቡም ጥልቅና የማይነበብ ነው ብዬ አሰብኩ። እንግዲያስ ትንሹና ምስኪን ሰው ለሰው ጥበቡንና እውነቱን እንድገልፅለት ከእግዚአብሔር ዘንድ ትልኬ መጣሁ እያለ ስለምን ይዋሻል? ፈጣሪ ታላቅነቱን እንድናውቅ ከሰጠን ህሊና ይልቅ እጅግ ዝቅ ያለና የተናቀ ግውዝ ባህሉን ካልሆነ በቀር ሊገልፅልን አይችልም። ጌታ ሆይ እኔ በፊትህ ደሀና ምስኪን ነኝ። ስላንተ የማይገባኝን እንዳውቅና ታላቅነትህን እንዳደንቅ አዲስ ምስጋናን ሁልጊዜ እንዳመሰግንህ ልቦና ሰጠኝ።

## <u>የዘርዓ ያቆብ ወደ እንፍራንዝ መግባት</u>

በ1625 ዓ.ም. ሱስንዮስ ሞቶ በርሱ ፋንታ ልጁ ፋሲለደስ ነገሰ። እርሱም በመጀመሪያ ፈረንጆቹን ወደ።

ግብፃውያንንም አላባረራቸውም በዚህ ምክንያት በኢትዮጵያ ሁሉ ሰላም ሆነ። የዚያን ጊዜ ከዋሻዬ ወጥቼ መጀመሪያ ወደአማራ አገሮች ሄድኩ። ኋላም ወደ በጌምድር ተመለስኩ። ለሁሉም በፈረንጆች ጠላትነት በሱስንዮስ ዘመን ከተባበሩት መነኩሳት አንዱ መሰልኳቸው። ስለዚህም ወደዱኝና ምግብና ልብስም ሰጡኝ። በዚህ ሁኔታ ከአገር ወደ አገር ስመላለስ የካህናቶቿን ክፋት አውቃለሁና ወደ አክሱም መመለስን አልወደድኩም። ሰው የሚሄድበትን ከእግዚአብሔር እንደሚታዘዝ አሰብኩ። ጌታ ሆይ የምሄድበትን መንገድና የምኖርበትን አገር ምራኝ አልኩት። ወደ ጎጃም ምድር ተሻግሬም ለመኖር አሰብኩ፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ወደ አላሰብኩት መራኝ። አንድ ቀን ወደ እንፍራንዝ አገር ወደ አንድ ጌታ ሰው የእግዚአብሄር ሀብት ነውና ሀብቱ ወደ ተባለ ደረስኩ። በዚያውም አንድ ቀን አደርኩ። በማግስቱም አክሱም ወዳሉት ዘመዶቼ ድብዳቤ እንድልክ ከእርሱ ቀለምና ወረቀት ለመንኩት። ይህ ሰውም

"አንተ ፀሐፊ ነህ ወይ?" አለኝ።

"አዎ ፀሐፊ ነኝ" አልኩት።

"ከኔ ጋር ጥቂት ቀን ተቀምጠህ የዳዊት መዝሙርን ጻፍልኝና ዋጋህን እሰጥሀለሁ" ብሎ ተናገረኝ።

"እሺ" አልኩት። የድካሜንም ፍሬ የምመገብበትን መንገድ ስላሳየኝ እግዚአብሔርን በልቤ አመሰገንኩት። እውነት ባስተምር ሰዎች ሊጠሉኝና ሊከሱኝ፣ ሊያባርሩኝ ካልሆነ አይሰሙኝምና ወደ ቀድሞ ሊቅነቴ ተመልሼ ሀሰትን ማስተማር ጠላሁ። እኔ ግን ከሰው ሁሉ ጋር

በፍቅርና በሰላም መኖርን ወደድሁ። በሃጥአን ቤት ከብሬ ከምኖር ግን ከሰው ተለይቼ የድካሜን ፍሬ እየተመገብኩ እግዚአብሔር በሰጠኝ ጥበብ ተሸሽጌ አልባሌ መስዬ መኖርን መረጥኩ። በጥቂት ጊዜም ቀለምና ብራና አዘጋጅቼ አንድ የዳዊት መዝሙር ፃፍኩ። ፅህፈቴም ያማረች ናትና ጌታዬ ሀብቱና ሁሉም አይተዋት ተደነቁ። ጌታዬ ሀብቱም ደሞዜን አንድ መልካም ልብስ ሰጠኝ፤ ደግሞም ወልደሚካኤል የተባለ የጌታዬ ሀብቱ ልጅ ላባቴ እንደፃፍከው ለእኔም ፃፍልኝ አለኝና ፃፍኩለት። አንድ በሬና ሁለት ፍየሎችም ሰጠኝ። ከዚህ በኋላ ብዙዎች ወደ እኔ ዘንድ መጥተው ዳዊትና ሌሎች መፅሐፍትን፣ ደብዳቤዎችን አፃፉ። በዚያ አገር ካለ እኔ በቀር ሌላ ፀሀፊ አልነበረምና ልብስ፣ ፍየሎች፣እህል፣ ጨውና ሌላም እነርሱን የመሳሰሉ ሰጡኝ። ለጌታዬ ሀብቱም አንድ ወልደ ገብርኤል ተሰማ የተባለና ሁለተኛ ወልደ ህይወት ምትኩ የተባሉ ሁለት ልጆች ነበሩት። አባታቸው ሀብቱም የሚበቃህን ምግብ እሰጥሃለሁና በእጅህ ጽፈህ የምታፈራውን ላንተ ይሆናልና፣ የዳዊትን ንባብ አስተምራቸው አለኝ። አባቴ ሆይ ያዘዝከኝን ሁሉ እሺ አድርጋለሁ አልኩት። ነገር ግን ካንተ በቀር ዘመድ የለኝምና በአባቴና በእናቴ ዘመዶችም ፋንታ ዘመድ ሁነኝ አልኩት።

## ስለ ህጋዊ የፈቃድ ጋብቻ

ይህ መንገድ ወደ አበሳ ይስባልና ሴት የሌለችው ወንድ ብቻውን ይኖር ዘንድ እንደማይገባው አወኩ። ለፊተኞቹ ሴት ታስፈልጋቸዋለች እንጂ ወንድ ብቻውን

ይኖር ዘንድ መልካም አይደለም፣ እንደተባለው በሰሩት ወጥመዳቸው እንዳይጠመዱ ሰዎች ተፈጥሮአቸውን ከደው ሊኖሩ አይገባቸውም። ጌታዬ ሀብቱንም የዘመኑን ክፋት ፈርቼ መሰልኩ እንጂ መነኩሴ አይደለሁም አልኩት። ለጌታዬም ሂሩት የተባለች አንዲት ቤተሰብ ነበረች። ምግባረ መልካምና ልባም፣ ትዕግስተኛ እንጂ ደም ግባታም አይደለችም። ጌታዬ ሀብቱንም

"ይህቺ ልጅ ሚስት እንድትሆነኝ ስጠኝ" አልኩት።

"እሺ ከእንግዲህ ባሪያህ እንጂ ባሪያዬ አይደለችም።"

"ሚስቴ ካልሆነች በስተቀር ባሪያዬ አይደለችም። ወንድና ሴት ብቻ በአንድ ስጋና በአንድ ንብረት ትክክል ናቸው እና ጌታና ባሪያ ልንላቸው አይገባም።" ጌታዬ ሀብቱ

"አንተስ የእግዚአብሔር ሰው ነህና እንደ ፈቃድህ አድርግ" አለኝ። ያቺንም ጠራትና እኔም

"ሚስቴ ልትሆኚ ትወጃለሽን" አልኳት።

"ጌታዬ እንደፈቀደ" አለችኝ። ጌታዬ ሀብቱም

" እኔስ እፈቅዳለሁ" አላት። እርሷም

"ከአንተ እሚበልጥ የት አገኛለሁ መልካም" አለችኝ። ጌታዬ ሀብቱንም

"አባታችን ሆይ ባርከን አልነው።"

"እግዚአብሔር ይባርካችሁ ይጠብቃችሁ። ለረዥም ጊዜ ፍቅርና ጤና ይስጣችሁ። ክፉ ነገርን ከእናንተ አርቆ በዚህ ዓለም ጥሪት ጋር ልጆች ይስጣችሁ" አለን። "አሜን" አልን። ይህቺም ሂሩት

ሚስቱ ሆነችና በጣም ወደደችኝ። በጌታዬ ሀብቱ ቤት የተናቀች ነበረችና፣ ቤተሰቦቹም ዘወትር ያሣዝኗት ስለነበሩ ዛሬ በጣም ተደሰተች። እኔም ስለወደደችኝ በተቻለኝ ሁሉ እንዳስደስታት በልቤ ወሰንኩ። እንደኛ ጋብቻ ከእግዚአብሔር የተባረከና በፍቅር የፀና ሌላ ጋብቻ እሚገኝ አይመስለኝም። ከአክሱም በሸሸሁ ጊዜ ከእኔ ጋ የወሰድኩት የቀረኝ ሁለት ወቄት ወርቅ ነበረኝ። በእጅ ፅህፈቴም ከብቶችና ፍየሎች፣ ልብስም አፈራሁ። በጌታዬ ሀብቱ ጎረቤትም ትንሽ ቤት ሰራሁ። ከዚያም ከሚስቴ ጋ በፍቅር ነበርኩ። እኔ እየፃፍኩ የጌታዬ ሀብቱን ልጆች ሳስተምር እርሷም ቀንና ሌሊት ትፈትል ነበር። ጌታዬ ሀብቱም ልጆቹን ስላስተማርኩለት በየወሩ አንድ እንስራ ጤፍ ይሰጠኝ ነበር። እንዲህ ብዬም ከሚስቴ ጋር በፍቅርና በመልካም ኑሮ አራት አመት ኖርኩ። በ1631 ዓ/ም ጥቅምት 11 ሰኞ ቀን ወንድ ልጅ ወለደችና በልጃችንም ተደሰትን። በፀጋ አባቴ በሆነው ስምም ሀብተ እግዚአብሔር ብዬ ሰየምኩት። ከሦስት ዓመት በኋላም አቡነ አልፎንዝ ወደ ሀገሩ ሄደ። ጠላቶቹም ሁሉ ተነሱ። ወዳጆቹ ከእርሱ ጋር ተሰደዱ። በዚያን ጊዜም የጥንት ትምህርት የሚያስተምሩ መምህራኖች በሀገር ሁሉ ተፈለጉ በአክሱም ያሉት ዘመዶቼም እንደቀድሞው በአክሱም ሆኜ ወደ ሊቅነቴ ተመልሼ መጽሐፍትን እንዳስተምር ፈለጉኝ። በአቡነ አልፎንዝ ጊዜ የነበረውን ስደት ፈርቼ የሸሸሁ ስለመሰላቸው ጠላቶችህ ጠፍተዋልና ወዳጆችህ ድነዋልና ወደ እኛ ተመለስ ብለው መልክተኞች ላኩብኝ። እኔም ጠላት የለኝም። ይህ የእግዚአብሔር ሰው ጌታዬ ሀብቱና ልጆቹ ሚስቴም ካልሆኑ በቀር ወዳጅም

የለኝም። ከቶም ልተዋቸው አልችልምና ለኔ ወደ እናንተ መመለስ አይሆንልኝም እናንተም በሰላም ኑሩ ብዬ መለስኳቸው። ይህም ግብዝ ጠላቴ መጀመሪያ ወደ ንጉስ ሱስንዮስ ያሳጣኝ ጠላቴ ወልደ ዮሐንስ አቡነ አልፎንዝ ከሄደ በኋላ ወደ ግብፃውያን ሃይማኖት ተመለሰ። ነገር ግን ለጊዜው የሚመቸው ካልሆነ በስተቀር ሃይማኖት የለውም። ነገስታት ግብዞችና ሽንጋዮችን ይወዳሉና በሽንገላው ብዛትም ወደ ንጉስ ፋሲለደስ ሄዶ ወዳጅ ሆነ። ወልደ ዮሐንስም እኔ በእንፍራንዝ አገር በሰላም እንዳለሁ ሰምቶ እንደገና እርሱ የፈረንጆቹ አስተማሪ ነበር። አሁንም ተሸሽጎ የፈረንጆችን ትምህርት ያስተምራል ብሎ ለእንፍራንዝ ሹም ነገረው። እኔም ስለሽንገላው በጣም አዘንኩ። መጀመሪያ ስለእኔ የፈረንጆች ጠላት ነው፣ በኋላም ወዳጃችን ነው አለ። ባዘነ ልቤም እግዚአብሔር የደላይን ከንፈሮች ይቆረጣቸው ብዬ በመዝሙር ለእግዚአብሔር ብዙ ቀን ፀለየኩ። እግዚአብሔርም ሰማኝ። ይህም ሰው በብዙዎች የደምቢያ አድባራት ላይ ተሾመ። ሰዎች ጠልተው ገደሉት። እሬሳውም በቤቱ ወድቆ ተገኘ። ገዳዩም አልተገኘም። ሹመቱና ገንዘቡንም ባእድ ወረሰው።

## በሃይማኖት ስለመጣው መቅሰፍትና የፋሲለደስ ታሪክ

በ1635 ዓ.ም በህዝብ ሐጢያት እና ፍቅረ-ቢስነት ፍቅር ማጣት በኢትዮጵያ ሁሉ ትልቅ እረሀብና ብርቱ መቅሰፍት ሆነ። ንጉስ ሱስንዮስንና የአቡነ አልፎንዝን ሃይማኖት የተቀበሉ ሃይማኖታቸውን ያልተቀበሉ

ወንድሞቻቸውን መጀመሪያ ገደሉ፣ አባረሩ። የተሰደዱትም በኋላ ከጠላቶቻቸው ብዙዎቹን ገደሉና አፀፋ መለሱ። በኋላቸውም ሆነ በፊታቸው የእግዚአብሔር ፍርሀት እንደሌለና የሰላምንም መንገድ እንዳላወቋት በግልፅ ታወቀ። በከንቱም ክርስቲያኖች ተባሉ። እየሱስ ክርስቶስ ግን ከሁሉ አስቀድሞና ከሁሉ በላይ ክርስቲያኖችን እርስ በርሳቸው እንዲፋቀሩ አዟቸዋል። ይህ ፍቅር የተባለው ግን ክርስቲያኖች በተባሉ መሀከል ፈፅሞ ጠፋ። ሁሉም ወንድሞቻቸውን ይበድላሉ። እርስ በርሳቸው እንደ እህል አበላል ይዋዋጣሉ። ፋሲለደስም በመልካም ምክርና ጥበብ መንገስ ጀመረ። ነገር ግን ደም በማፍሰስ አመፀኛ ንጉስ ሆኖ በክፋቱ ፀና እንጂ መልካሙን አልመረጠም። መንግስቱን በመልካም ጥበብ ያበጁለትን መልካም ቤቶችና ምሽጎችን የሰሩለትን ፈረንጆች ጠላቸውና አባረራቸው። በመልካም ፋንታ ክፉ መለሰላቸው። ይህም ፋሲለደስ በሁሉም ክፉ አድራጊ ሆነ። ሰዎችንም አለ ፍቅር አለ ፍርድ ገደለ። ዝሙትንም አበዛ። ሴቶችን ዝሙቱን ከፈፀመባቸው በኋላ ገደላቸው። አመፅ የሚሰሩ ሰራዊቶችን ሁሉ እየሰደደ የድሆችን ቤትና አገሮች አስወረረ። እግዚአብሔር ለክፉዎች ሕዝቦች ክፉ ንጉስ ሰጣቸው። በንጉሱና በሕዝቡ ሐጢአትም ረሀብና መቅሰፍት መጣ። ከረሀብ በኋላ ቸነፈር ሆነና ብዙዎቹ ሞቱ። ሌሎችም ለመዳን ያልሆነ ፍርሀት ፈሩ። በእብደታቸው ፀንተዋልና ግማሾቹ አቡነ አልፎንዞን ስላባረራችሁት የእግዚአብሔር መቅሰፍት በላያችሁ መጣ አሉ። ግማሾቹ ደግሞ የቀድሞዋን ሃይማኖት ስለከዳችሁ

ቤተክርስቲያንን ስላረከሳችሁ ይህ መቅሰፍት መጣ እየተባባሉ እርስ በርሳቸው ተጣልተው ተለያዩ። እግዚአብሔር ለሁሉ ፍጥረት የሰራውን እውነተኛውን ስራ ፍቅረ-ቢስ የሰው ስርዓት ስላፈረሱና ስለተላለፉ መቅሰፍት እንደመጣባቸው አላወቁም። ሃይማኖት እንዲህ ነው ወይም እንዲያ ነው የሚለውን ስለሰው ሕግጋት ሲሉ ዋና ዋና ህግጋትን ሻሩ። የኢሳያስ ወንጌልም ስለነርሱ ተናገረ።

"እነዚህ ሕዝቦች በአፋቸው ያከብሩኛል። በልባቸው ግን ከእኔ እጅግ ይርቃሉ። የሰውን ስርዓትና ትምህርት እያስተማሩም በከንቱ አመለኩኝ" አለ። ደግሞ ዮሐንስም

"በብርሀን አለሁ እያለ ወንድሙን የሚጠላ ዋሾ ነውና እስከ ዛሬም በጨለማ ይኖራል። ወንድሙን የሚወድ ግን በብርሀን ይኖራል። በእርሱ ዘንድ እንቅፋት የለም። ወንድሙን የሚጠላ ደግሞ አይኖቹን ጨለማ አሳውሮታልና በጨለማ ይመላለሳል። ወዴት እንደሚሄድ አያውቅም።" አለ። ይም ትንቢት በሀገራችን ሰዎች ላይ ተፈፀመ። የሚሄዱበትን አያውቁምና ስለሃይማኖቻው ይጣላሉ። የሚምኑትን አያውቁትምና በጨለማ ይኖራሉ። እኛ ግን በረሀብ ጊዜ ወርቃችን ካለቀ በኋላ እግዚአብሔር ምስጋና ይድረሰው ከብቶቻችንና ልብሶቻችንን ሸጠን በላንና የተራቡትን፣ የታመሙትን አበላን እንጂ እንደ ሌሎቹ አልተራብንም። አራት አመት የሆነው ረሀብና ቸነፈር አልተራብንም አልታመምንም። በክፉ ቀኖች አያፍሩም በረሀብ ጊዜም ይጠግባሉ የተባለው በእኛ ላይ

ተፈፀመ፡፡ ቁጥር የሌለው መልካምም ለኛ ስላደረገልን እግዚአብሔር አመሰገንነው፡፡

## ስለጌታዬ ሀብቱ ሞትና የልጁ ታሪክ

ካንድ ዓመት በኋላ ጌታዬ ሀብቱ ሞተብንና እጅግ አዘንን፡፡፡ ትልቅ ለቅሶ አለቀስን እሱ ሳይሞት ጠርቶ ይኸው እኔ እሞታለሁ እግዚአብሔር ይጠብቃችሁ ይባርካችሁና አንተም ለልጆቼ አባት ሁናቸው አለኝ፡፡ አንድ በሬና እንደ በቅሎ ሰጠኝ፡፡ ለሚስቴም ሁለት ላሞች ከነልጆቻቸው ሰጣት፡፡ ስለነፍሴ ፀልዩ ብሎንም በእግዚአብሔር ሰላም ሞተ፡፡ እርሱ በተባረከች ነፍሱ አረፈና በትልቅ ክብርም ቀበርነው፡፡ የበኩር ልጁ ወልደ ሚካኤል የተባለውም እንደ አባቱ ወደደኝ፡፡ ምክሬንም ይሰማ ነበር፡፡ ስሟ ወለተ ጴጥሮስ ፈንታዬ የተባለች ሚስትም ነበረችው፡፡ እርሷም የከበረች የክቡራን ወገኖች ነበረች፡፡ መልካም ምግባርና ወዳጅ ትህትና የሞላች ናት፡፡ እናት ልጅዋን እንደምትወድ ትወደን ነበር፡፡ ሁለቱ የጌታዬ ሀብቱ ልጆች ተሰማና ምትኩ አድገው ዳዊት ማንበብ አወቁ፡፡ ምትኩ ግን እንደገና ሰዋሰው መፃህፍት አወቀና በጽኑ ፍቅርና ከእኔ ጋር አንድነት ያለው ሆነ፡፡ እርሱ ሚስጥሬን ሁሉ ያውቃል፡፡ ለእርሱ የሸሸኩት የለም፡፡ ብዙ ጊዜ ከለመነኝ በኋላ ስለርሱ ፍቅር ብዬ ይህቺን ትንሽ መጽሐፍ ፃፍኩ፡፡

## የዘርዓ ያዕቆብ የፍፃሜ ታሪክ

ልጄም አድጎ ያማረ ጎበዝ ሆነ፡፡ ሃያ ዓመትም በሆነ ጊዜ እርሱ ባለማወቅ ወደ ምንኩስና እንዳዘነበለ

አወቅሁ:: "ይህ ሥራ ፈጣሪ ለኛ የሰራልንን ስርዓት ያፈርሳልና አይገባም ብዬ ብዙ ተቆጣሁ:: " ነገር ግን በተፈጥሮአችን ሥርዓት ሚስት አግብተህ ኑር አልኩት::

"እሺ ሚስት ስጠኝ" አለኝ:: ላምጌ ከተባለው አገር መድሃኒት የተባለች የአርብቶ አደሮቹን አለቃ ያማረች ልጅ ፈልጌ አገኘሁ:: ልጅም በርሷ ተደሰተ:: አባቷም አስራ አምስት ከብቶችና ልብሶች ሰጣት:: የልጅም ሚስት ሆነችው አብረው በፍቅር ነበሩ:: ከሁለት ዓመት በኋላ ወንድ ልጅ ወለደች:: እግዚአብሔርም ይባረክ ብየ ይትባረክ አልኩት:: እንደገናም ወንድ ልጅ ወለደች:: ደስታዬ አልኩት:: መልሳም ሴት ወለደች:: ዋጋዬ አልኳት:: ከመልካም ሁሉ ያጠገበኝ እግዚአብሔርን አመሰገንኩት:: እኔም ለሰዎች ክርስቲያን እመስላቸው ነበር:: ነገር ግን በልቤ እርሱ እንዳስታወቀኝ የሁሉ ፈጣሪና የሁሉ ጠባቂ በሆነ በእግዚአብሔር ካልሆነ በስተቀር በማንም አላምንም:: አማኝ ሳልሆን አማኝ እመስላለሁ:: በእግዚአብሔር ዘንድ ይህ ያስቀጣኝ ይሆን? ብዬ አሰብኩ:: ሰዎችን እንዲህ አታልላቸዋለሁ:: ሰዎችን ማታለል ይገባልን? አልኩ:: እውነቱን ብነግራቸው ለስዎች ትልቅ ጥፋት ካልሆነ በስተቀር ሃሳቤን መግለጼ ጥቅም የለውም:: ሊሰድቡኝና ሊያባርሩኝ ካልሆነ በስተቀር አይሰሙኝም:: ስለዚህ እነርሱን መስዬ ከሰው ጋር እኖራለሁ አልኩ:: እርሱ እንዳስታወቀኝ በእግዚአብሔር ዘንድ ኖርኩ:: ከኔ በኋላ የሚመጡ እንዲያውቁ ግን እስከሞት ድረስ በእኔ ዘንድ ሸሽጌ የምይዘውን ይህን መጽሐፍ በተማሪዬ ገፋፊነት ልፅፍ ወደድኩ:: ከሞቴ በኋላ አዋቂና መርማሪ ሰው ቢገኝ ግን በሃሳቤ ላይ

ሃሳቡን እንዲጨምርበት እለምነዋለሁ። ይኸው እኔ ከዚህ በፊት ያልተመረመረውን መመርመር ጀመርኩ። የሃገራችን ሰዎች በእግዚአብሔር ረድኤት አዋቂዎች እንዲሆኑ፣ እውነትንም ወደ ማወቅ እንዲደርሱ፣ ሐሰትን እንዳይፈልጓትና እመፃንም ተስፋ አድርገው ዝም ብለው ከከንቱ ወደ ከንቱ እንዳይሄዱ እውነትን እንዲያውቁና ወንድሞቻቸውን እንዲወዱ፣ እንግዲህ እስከአሁን እንደሚያደርጉት በከንቱ በሃይማኖታቸው እንዳይጣሉ እኔ የጀመርኩትን አንተ ጨርሰው ይህንን ያወቀና ከዚህም የተሻለ እሚያውቅ ቢገኝ ያስተምረውና ይፃፈው። እግዚአብሔር እንደ ልቡ ይስጠው። ፈቃዱን ሁሉ ይፈጽምለት። እኔ እንዳጠገበኝ ሥፍር በሌላው መልካምም ያጥግበው። እኔን እስከ ዛሬ ብፁዕ አድርጎ እንዳስደሰተኝ በዚህ ምድር ብፁዕ አድርጎ ያስደሰተው። በዚህ መጽሀፌ ከኔ በላይ እሚሳደብና እንዲያምርለት የሚፈልግ ግን እግዚአብሔር እንደ ምግባሩ ይሰጠው አሜን። የዘርያዕቆብ መጽሐፍ ተፈፀመ።

## የዘርአ ያዕቆብ መጽሐፍና አባ ጁስቶ ዳ ኡርቢኖ የካርሎ ኮንቲ ሮሲኒ ማስታወሻ

መጽሀሐፈ ዘርአ ያዕቆብና መጽሐፈ ወልደ ሕይወት የተባሉ በጣም ልዩ የሆኑ ሁለት የኢትዮጵያ ጽሁፎችን ኤኖ ሊትማን በ1904 አሳተመ። እነዚህ ጽሁፎችም ቤተ ክርስቲያናዊ በመሆናቸው አሳዛኝ ከሆነው የኢትዮጵያ ስነጽሁፍ በይዞታቸው መለየታቸው እንግዳ ነገር ሲሆን፣ በመጻሕፍቱ በአንደኛ ዘርአ ያዕቆብ

በአክሱም ተወልዶ ፖርቱጋሎች ተዋሕዶዎችን ያሳድዱ በነበረ ጊዜ ተሰዶ የደረሰበትን እምነቱን ይገልጻል* የክርስቲያኖች የአይሁድና የእስላሞችን ሕጎች እያነጻጸረ ይተችና በውስጣቸው ጉድለት ስላለባቸው ከእግዚአብሔር የተገኙ ናቸው ለማለት አለመቻሉን ገልጾ ሁሉንም አልቀበል ብሎ ስለ አምላክ ብቻ ሀሳብ ወደ መቀበል ደረሰ* ደቀመዛሙሩ ወልደ ሕይወትም ትምህርቱን ይዘረጋል:: ዳባዲ ስለ መጻሕፍቱ ባዘጋጀው ካታሎግ ባጭሩ ባመለከተውም ጽሑፎቹ የሊቃውንቱን አእምሮ ቀስቅሰው ነበረ:: ቱራዬብ ባንድ ማስታወሻው ስለ እነሱ ጽፎ ነበር ግን ባጻጻፉ ምክንያትም ውጤቱ ኢምንት ነበር* አንዱን እትሙን ጀርመናዊው ሊቅ ያሳተመው አስረሳው::

እንከን የሌለበት የሊትማን እትምም የኢትዮጵያን ጉዳዮች በመከታተሉ ዘንድ በታላቅ ደስታ ተቀባይነት አግኝቶ ብዙ የሊቃውንትን ትችት የማግኘት ክብር ተሰጠው:: እምነቱ ስውር የቅዱሳት መጻሕፍት አተረጓጓም የቢዛንሱን አተረጓጎም የተከተለ በመሆኑ በነፃ አስተሳሰብ ማለፉ ምናልባት የማይቻል ክልል በመሆኑ በኢትዮጵያ እንደምን ታለመ ብሎ ማሰብ እንኳ አዳጋች ስለሆነብን የዘርአ ያዕቆብ ናቸው የተባሉት ሀሳቦች ከኢትዮጵያ የሚጠበቁ አልነበሩም:: በሌላው በኩል ደግሞ የዘርአ ያዕቆብ ጽሁፍ ይኸን እንግዳ ሕገ ወጥ ሁኔታ አሳየ* የደራሲው ቃል ረጅም ዕድሜው ያንድ ደቀመዝሙሩ ጽሁፍም በእምፍራዝ እና በአቅራቢያው በሚገኙ የበጌምድር አውራጃዎች አንድ ትምህርት ቤት በእውነቱ አቋቁሞ ትምህርት ቤቱ ጥቂት ጊዜ የቆየ

መሆኑን በገለጸልን፡፡ ነገር ግን ስለዚህ ትምህርት ቤትና ስለ አቋቋመው ሰው ሌላ ዜና አልተገኘም፡፡ አውጥቶ አውርዶ የደረሰባቸው የራሱ ሃሳብ ፍሬ መሆናቸውን ቢናገርም የዘርአ ያዕቆብ ሀሳቦች ሕገ ወጥነት ከኢትዮጵያ ውጭ የመነጩ ሃሳቦቹ ይሆኑን ብሎ ወደ መጠየቅ አደረሰ፡፡ ሊትማን በዚሁ ሳይጠራጠር የዐረቢኛ ስሜት ወደ ማግኘቱ ያዘነብላል* ሌሎችም ሌላ ስሜትን ያስባሉ ለምሳሌ ኢየሱሳውያን ሲባረሩ ወደ ኢትዮጵያ ገብቶ ጥቂት ዓመታት ለመቀመጥና ለማስተማር የቻለውን ፕሮቴስታንቱ ጴጥሮስ ሃይሊንግን የመሰለ፡፡

ዳባዲ የሰበሰባቸውን በእጅ የተፃፉ መፃህፍት በመረመርኩ ጊዜ ከሁለት ሐተታዎች ዋናው የእጅ ጽሁፍ የ17ኛው ወይም የ18ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መባቻ መሆኑ ቀርቶ የ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መስሎ በማግኘቴ በጣም ተገረምኩ፡፡ እንደዚህ በገሀድ የክሕደት የሆኑ መጻሕፍት እንደምን አሁንም ገልባጮች አገኙ፡፡ እስከ ዘመናችን አቅራቢያ ድረስ ባንዳንድ የጣና ገዳም የቆየው ወደ ክህደት የተጠጋና ነጻ ሀሳብ ይሆን? የእጅ ጽሁፉ አንድ ሌላ ቅጂ አባጁስቶ ዳ ኡርቢኖ የገለበጠው፣ ለአንቷን ዳባዲ ከደብር ታቦር በየካቲት 28/1853 የጻፈው ደብዳቤ ሸኚ ነበረው፡፡ ስለ መፅሀፉ ጠቃሚ ዜና የያዘ በመሆኑም በሞላ አሳትሜው ነበረ* አባ ጁስቶ ካመታት በፊት አንድ የተቀዳደደ መጽሐፍ ማየቱንና በኋላም ሙሉውን መጽሐፉ ወደ ደምብያ ዘምቶ ከተመለሰ ወታደር ማግኘቱን ይገልፃል፡፡ ይህ ስመ ክሕነቱ አባ ጁስቶ ዳ ኡርቢኖ የሆነ ሰው በማታርያ /ሉካ አውራጃ/ ለጁዜፔ ኩርቶፖሲ እና ለቴሬዛ ስኮለስቲካ ጎዲ በነሐሴ

20/1814 ተወለደ። የክርስትና ስሙም ያዕቆብ /Jacopo/ ነበረ። ልጅነቱን በሊቮርኖ አሳልፎ የሚወዳት ልጁ ስለሞተች ገና ልጅ ሳለ የቅዱስ ፍራንሲስን ልብሰ መነኮስ ተቀብሎ ምንኩስናውን ለተቀበለበት ለቼንጎሊ ገዳም አበ ምኔት ለአባ ጁስቶ ዳ ካመሪኖ ክብር እና በዚያን ጊዜ በማርክ አውራጃ ያውራጃ ካሕን ለነበረው ለአባ ፍራንቼስኮ ዳ ኡርቢኖ ክብር ጁስቶ ዳ ኡርቢኖ ተባለ። ወደ ፎሶምበሮነ በመዛወሩ ተማርሮ ወደ ሚስዮን ስራ እንዲዛወር ጠየቀ* በመጋቢት ወር 1845 ወደ ሮማ መጥቶ የፈረንሣይና የአረቡን ቋንቋ ተግቶ አጠና* ከዚያም ለኢትዮጵያው ሚስዮን ከማሳያ /አባ ማስያስ/ ጓደኝነት ተመርጦ ግንቦት 14/1846 በቺቪታቬክያ በመርከብ ተሳፍሮ በታህሣሥ መባቻ ምጽዋ ደረሰ። ብዙ ወራት በዳጋሜ ተቀመጠ። ከዚያም በበጌምድር ሰፈረ። በግንቦት ወር 1855 አቡነ ሰላማ ካገር እንዲወጣ አድርጎት በስናር በኩል ወጣ። የአቡን ማእረግ ቢሰጠው ጊዜ አልተቀበለውም። በሚያዝያ 1856 ከካይሮ ወደ ሱዳን መምጣት ፈለገ። ነገር ግን በዚሁ ዓመት በህዳር 22 ቀን በካርቱም ሞተ።

አባ ጁስቶ ኢትዮጵያንና ግዕዝን በጣም ያፈቅር ነበር። "ኢትዮጵያ ከአውሮጳ ይበልጣል በጌምድርም ከኢጣልያ በበለጠ ዋጋ አለው" ብሎ በየካቲት 17/1850 በጎንደር ጻፈ። በጥቅምት 26 ቀንም "በአረመኔነትና በሰብአዊነት በጭቆና እና በነፃነት ኢትዮጵያ ከኢጣሊያ ትበልጣለች ብሎ ጻፈ። ስለ ጥናቱ የካቲት 17/1850 በኢጣልያ ለሚገኘው ወዳጁ ስለትምህርቱ እንዲህ ሲል ጻፈ* "ዐመቱ ወደ ክረምት /የኛ በጋ/ አለፈ የምሰራው

ስለሌለም ያገሩን ቅዱስ ቋንቋ እና ድርሰት ማጥናቱን ያዝኩ*ተስፋ ካደረግሁት የበለጠም ጥቅም አገኘሁ። ድርሰቱ አብዛኛው ሃይማኖታዊ ቢሆንም ለታሪክ ሆነ በጣም ከሰለጠኑት የዘመናችን ኤውሮጳ ሰዎች ያልተሻሉ ደግሞም ያልባሱ የማንኛቸውንም ዘመን ሰዎች የሀሳብ ጉዞ ለማወቅ በጣም ጠቃሚ ነው። በግንቦት 26/1852 ከደብረ ታቦር በጻፈው ደብዳቤም ብዙ ጥናት ካባባሰው የዐይን ሕመም መሰቃየቱን እየጻፈ እንዲህ ይላል*

"የኢትዮጵያ ልሳነ መፅሐፍ አንድ ትልቅ ሰዋሰውና አንድ ትልቅ መዝገበ ቃላት ጽፌአለሁ።...እስከዚህ ድረስ በሮማይስጥ ጽፌአለሁ።... ሁለቱን የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ይኸውም ጥንታዊውንና ዛሬ የሚነገርበትን ፈረንሳዊ እንግሊዛዊ ወይም ኢጣልያን ይሁን ከማንኛውም ኤውሮጳዊ ይበልጥ የማውቅ ለመሆኔ መመካት እችላለሁ። ከዘመናዊው ይልቅ በጥንታዊው የኢትዮጵያ ቋንቋ የተጻፈውን ማድመጥ የኢትዮጵያውያን ባሕሪ ስለሆነ ለሚስዮን የሚያገለግል ምናምን በመፃፍ ላይ ነኝ።

"በሚያዝያ 26/1855 በአቡነ ሰላማ ትእዛዝ ሲታሰር እንዲህ ይላል

"በጎጆዬ ውስጥ ሆኜ በግዕዙ መዝገበ ቃላቱ የሚጨመር አንዳንድ ነገር እጽፍ ነበረ።" ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያ ነክ ጥናት የነበረው ፍቅር ከዋናው ተግባሩ ይኸውም ወደ ኦሮሞዎች ሚስዮን ከመዛወር እስከ ማፈግፈግ አደረሰው። በነሐሴ 1852 ካርዲናል ማሳያ /አባ ማስያስ/ በይፋግ አግኝቶት እንዲህ ሲል ጻፈ

"ከንግግራችን ኢትዮጵያን ከመጠን በላይ መውደዱንና ወደ እውነተኛው ሚስዮኖችን ወደ

አሮሞዎች አገር ሊከተለኝ እምብዛም የማይፈቅድ መስሎ ስለታየኝ ከልቤ አዘንኩ። ... በኢትዮጵያ ጥንታዊ ቋንቋ ፍቅር ልቡ ተይዞ ነበር። የዚህ ቋንቋ ጥልቅ ፍቅር ነበረው ደግሞም እውነቱን ለመናገር በጣም ገፍቶበት ነበረ። እዚያ ከደረስን አንስቶ አሮምኛን በማጥናት ፈንታ ግዕዝን ያጠና ነበር* የሐዋርያ ግዴታዎችን ችላ እስከ ማለት ድረስም በጋለ መንፈስ ይተጋበት ነበረ። ይህን ጥናትም ብልሹና ጠማማ ከሆነው ከደብተሮቹ ወገን ጋር ማገናኘቱ አልቀረም* ተግባሩን ከመፈጸም ከማራቃቸውም በላይ ፈፅሞ እንዳያበላሹብኝ በጣም የሚያሰጋ ነበረ። ወደ አሮሞዎች ሚስዮን ለመሳብ ከዚያ ቀጥሎ የተደረገ ሙከራም ሳይሳካ ቀረ። ማስያስ እንዲህ ብሎ ይናገራል*ሚስዮናውያን እጅግ ማስፈለጋቸውን አይቼ አባ ጁስቶ ወደ ሚስዮን እንዲመጣ ለማድረግ የመጨረሻ ጥረት ለማድረግ ፈለግኩ።... እርሱ የሚወደውን የግዕዝን ቋንቋ በማጥናት በሞላው ተይዞ በቤተልሔም ይቀመጥ ነበር። የፍቅርና የማደፋፈሪያ ደብዳቤ ጻፍኩለት። ነገር ግን ይህን አባታዊ ጥሪንም አላዳመጠም። ለኢትዮጵያና ለቋንቋዋ በነበረው ፍቅር ይሁን ወይ በሌላ ከዚያ አገር መነቃነቅ አልፈለገም።"

ጁስቶ ዳ ኡርቢኖ ለግዕዝ ስለነበረው ፍቅርም በዱሮ የሕግ ሊቃውንት አነጋገር የማስረጃ ማስረጃው በፓሪስ ብሔራዊ ቤተ መጻህፍት በሚገኙ በአንዳንድ ጽሁፎቹ ይገኛል። ከነዚህም አንዱ በጥንቃቄ ያዘጋጀው መዝገበ ቃላት ነው። እነዚህ ጽሁፎችም ያን ቋንቋ አሳምሮ ያውቀው እንደነበረ ያሳያሉ። ከካቶሊክ ሚስዮኖች ጋር ስለ ነበረው ግንኙነት በ19 መቶ ክፍለ ዘመን

በኢትዮጵያ ታሪክ የደረሰውን አንድ ሁኔታ ከመጥቀሴ በፊት አባ ጁስቶ ስለ ኢትዮጵያ ስላደረጋቸው ጥናቶች ማብራራት አስፈላጊ ሆኖ ታየኝ። ሁኔታውን የተናገረውም የአቡነ ጃኮቢስ ተከታይ ሊቁ ኢትዮጵያዊው የካቶሊክ ካህን ስመ ጥሩው ተክለ ሃይማኖት ነው። አቡነ ስላማ እና አፄ ቴዎድሮስ አባ ጁስቶን ካገር ስለ ማስወጣታቸው ተርኮ ሲያበቃ እንዲህ ሲል ይቀጥላል። "አባ ጁስቶ ስማቸው ከተጠራው ከቤተልሄሙ ደብተራ አማርኮኝ እና ከሊቀ ካህናት ጎሹ ጋር በበጌምድር በነበሩበት ጊዜ ፍራማሶን የተባሉት የከሐዲያን መጥፎ ትምህርት ያለበትን አንድ መጽሐፍ ገዝቶ አባዝቶ ለወዳጆቹ ሰጠ። የመጽሐፍ ርዕስ "ወርቄ" ነበረ። አንዳንድ ያዩ እንደሚሉትም መጽሐፉን ራሱ ጽፎ በልበ ወለድ የወርቄ አለው እንጂ የወርቄ አልነበረም። እውነቱም እሱ/አባ ጁስቶ/ ሊቅና የቅዱሳት መጻሕፍትን ትርጉምና ፍልስፍናን የሚያውቅ ነበረ* ከዚሁም በላይ ሃይማኖታዊ ቅኔዎችን እስከ መቀኘት ድረስ አማርኛንና ግዕዝን ባጭር ጊዜ ውስጥ አጥንቶ ነበረ።"

"ወርቄ የሐተታ ዘርአ ያዕቆብ" ሌላ አርእስ ነው* የተነገረውም ስለዚሁ መሆኑንና አባዝቶ ለወዳጆቹ የላካቸውና ለዳባዲ ወደ ፈረንሣይ አገር የላካቸውና ከዚያው መሆናቸው ሊጠረጠር አይቻልም።

"መጽሃፈ ዘርአ ያዕቆብ የአባ ጁስቶ መሆኑ በድንገት መነገሩም ለብዙ ጊዜ አጠራጥሮኝ ነበረ*ይህን ጥርጣሬዬንም ሳልደብቅ ስለ ተጠቀሰው የተክለሃይማኖት ጽሁፍ ማስታወሻ ስጽፍ ጥርጣሬዬን ሊደግፉት የሚችሉ አንዳንድ አንቀጾች አቅርቤአለሁ።"

ከሁሉ አስቀድሞ ያዕቆብ መሆኑን ያመለከትኩት ራስ የአባ ጀስቶ የክርስትና ስም ከመጽሐፉ ደራሲ ስም ጋር ይገናኛል። ትርጉሙም "የያዕቆብ ዘር" ማለት ነው።

ደግሞም ከዚህ ቀድሞ እንዳመለከትሁት ሁሉም የእጅ ጽሁፉ /መጽሐፍ/ የቅርብ ጊዜ መሆኑ አሳሳቢ ነው። አባ ጀስቶ በፔዛሮ ፍልስፍና እንዲያስተምር መመረጡም በቂ ችሎታ እንደነበረው ያስረዳል። ግዕዝን አሳምሮ ያውቅ እንደ ነበረም ተመልክተናል* በፓሪስ ብሔራዊ ቤተ መጻሕፍት የሚገኙት ቅኔዎቹም ቋንቋውን በደንብ ይፅፍ እንደ ነበረ ያሳያሉ።

አስቸጋሪ መስሎ የሚታየው አንድ ካቶሊካዊ ሚስዮናዊ የክርስቲያን ያልሆነውን መጽሐፍ መዘርጋቱ ነው። በከባድ ኀዘን ምሬት ምክንያት አባ ጀስቶ መመንኮሱ የታወቀ ነው። ሆኖም ተፈጥሮው ንቁ ብርቱና ጥብቅ ሆኖ በጣም ይቆጭ እንደ ነበረ በሐዘንተኛነቱ ይታይ ነበረ። ለናሺምቤኒ የፃፋቸው ደብዳቤዎች እንደሚያረጋግጡትም በአፍሪቃ ሆኖም ይሰቃይ ነበረ።

ወደ ካርቱም አደገኛውን ጉዞ ከመፈፀሙ ጥቂት ቀደም ብሎ በመጋቢት 31/1856 የፃፈው ደብዳቤ በተለይ

"አይደለም ሐዘንተኛ አይደለሁም ኀበዝ ነኝ ስቃይና አደጋም አልፈራም ወዳጄ ሆይ ስለ ሞትም እንደሆነ ብዙዎች አንጎሎችን የሚያዞረውና ከጀርባው ምን እንዳለ ማንም ሊገምት የማይችለውን ያን ትልቅ መጋረጃ ሲነሳ ለማየት በመጠኑ እፈልጋለሁ። ይህ የማወቅ ፍላጎትም ዱሮ አንተን ይዞህ የነበረው ነው* ከጥቂት ዓመታት ወዲህም እኔን በጽኑ ይዞኛል። ይህ መጋረጃ መገንጠል ይህ በትልቁ "ሠሪ" ላይ ድፍረት

እንዳይሆን እፈራለሁ* ብዙዎችንም ስለዚህ ድፍረት ግድ የሌላቸው መሆናቸውን አውቃለሁ* ሆኖም እኛ በጣም ትንንሾች ብንሆንም የ"ትልቁን" ዓላማ በቀላሉ እንዳንደፍር አእምሮ ይጠይቀናል::" እነዚህ ቃላትና ንግግር የሚስዮናዊ አይደሉም አልልም:: የክርስቲያኖች ናቸውም አልልም:: አባ ጄስቶ ለናሺምቤኒ የጻፋቸውን ደብዳቤዎች ያሳተመው ታርዱቺ የመነኩሴውን የመንፈስ አካሄድ አሳምሮ ይገልጻል* አባ ጄስቶ በሃሳብና በጥናት ለተዋጠና በልቡ ውስጥ ሲያበራ የነበረው የእምነት ነበልባል ሲደክም ችላ አለው:: ይህ እየጎደለ በሄደ መጠንም አእምሮው መጨረሻ በሌለው በሀሳብ ጠፈር ውስጥ ነጻ ሆኖ ይበር ነበረ:: ነገር ግን በዚህ በረራ ነጻነት ማየት ማመዛዘን እያንዳንዱንም ነገር ማነጣጠር ባስፈለገ ጊዜ መፍትሄ በማይገኝለት ችግርና ጥርጣሬ ውስጥ መውደቁ አልቀረም:: ወደ መጨረሻ ጊዜም በመንፈሱ ላይ የነበረው የማሣያ ተጽዕኖ እየደከመ በሄደበትና የርጎራኄ ሚስዮን ስሜቱ በቀዘቀዘበት ጊዜ በጥናትና ምርምር ተዋጠና የሐዋርያዊ አገልግሎት ማለዘቢያ ወይም መግቻ ባለመኖሩ በግልፅ ወደ መመርመሩ ጉዳይ ተገፍቶ የተፈጥሮው ከሆነው ሁሉን መመልከቱና ለሁሉም ምክንያት መፈለጉ አደገኛ ወደ ሆነ መነጻጸረና ምርመራ ውስጥ መራው ታርዱቺ እንዲህ ይላል::

መጀመሪያ ከተማረው እንዲህ ቢርቅም አባ ጄስቶ እምነቱ ሲያወላውል ነፍሱ በአሳዛኝ ጥረጣሬ ሲያዝም አንድ ከሁሉ በላይ የሆነ አእምሮ:: አንድ ለሁሉ የሚያስብ ህላዌ የመኖሩ እምነቱን ሳያጓድል ይዞ በደብዳቤዎቹ ሁልጊዜ ያስታውስ ነበረ:: ታርዱቺ ቀጥሎ

እንደሚለውም የክህነትን ስርዓትና ትምህርተ ሃይማኖት በኢትዮጵያ ቋንቋና ስነ-ጽሑፍ ማወቁን ተገንዘቦ ማሳያስ ያቀረበለትን የአቡን ማዕረግ አልቀበል ያለበትን ምክንያት ይኸው ይገልጸዋል። ከዚህ በጣም በተሻለ መንገድ የሚገልፀው ግን ያው "መጽሐፈ ዘርአ ያዕቆብ" ራሱ ነው አባተክለሃይማኖት እንደ ተናገረው ምስኪኑ መነኩሴ በባዕድ ቋንቋና በሀሰትም ስም የመንፈሱን ሐዘን ማውጫ ፈልጎበት ይሆናል የተባለው ነው።

ስለነዚህ ወሬዎች መሠረት የነበረኝን ጥርጣሬ አንድ የመጨረሻ ማስረጃ ያስወግድልኛል።

አባ ማስያስ እንዲህ ሲል ይፅፋል* "በይፋግ ሳለሁ አባ ጁስቶ ግዕዝ አስቸጋሪው በነበሩበት ዓመታት ካደረገው ጥናት አንዳንድ ጽሁፍ ለዓይነት አመጣልኝ*ይኸውም በአንድ ሙፍቲ አንድ ቃዲ አንድ ሚስዮናዊ እና በአንዲት የ"ካሪታ" መነኩሲት መካከል የተደረገ ንግግርን አንድ ፈረንሳዊ ሚስዮናዊ የፃፈውን አርእስቱም "የቅርጣሳሚታዎች" የሚለውን ወደ አገሩ ቋንቋ የተተረጎመውን ትንሽ መጽሐፍ ነበረ። ይኸን መጽሐፍ በ "ፕሮፓጋንዳ" /ሮማ/ አግኝቼ የእስልምና ሃይማኖት ብዙ ይስፋፋ በነበረበት በኢትዮጵያ ብዙ ይረዳ ይሆናል በማለት ወደ አገሩ ቋንቋ እንዲተረጉመው የላክሁለት እኔው ነበርሁ። በእውነትም ይህ መጽሐፍ በሕዘብ ዘንድ ተወዳጅነት አገኘና ባጭር ጊዜ ውስጥ ብዙ ተራባ። ሁሉም "ሙፍቲ" ብለው ይጠሩት ነበረ። "በግንቦት 26/1852 ከደብረ ታቦር በጻፈው ደብዳቤም አባ ጁስቶ ስለዚህ ትርጉም ይናገራል።

ይህ መጽሐፍ ርእሰ ደብር ቡርጋድ የጻፈው እና ስመ ጥሩው አታሚ ፊርመን ዲዶ በፓሪስ በ1847 ዓ.ም ያሳተመው ነው* አርእስቱም "የቅርጣሳማቲዎች ወይም ባንድ የካቶሊክ ቄስ አንድ ሙፍቲ እና አንድ ቃዲ መካከል የተደረገ ንግግር" የሚል 192 ገጽ ያለው ቅጹ 12 የሆነ መጽሐፍ ነው። የክርስትያን ሃይማኖት ከእስላሙ የሚበልጥ መሆኑን የሚገልፅ ሆኖ መንፈሱ ግን ከ "ሐተታ"ው በመሠረት የተለየ ነው። ነገር ግን በችኮላ ለመረመረው እንኳ በሁለቱ መጻሕፍት መካከል ያለው እውቂያ ጉልቶ ይታያል።

"መጽሐፈ ዘርአ ያዕቆብን" መጀመሪያ ካነበብኩት ጊዜ አንስቶ ስለ እስላም ሃይማኖት የሚያሳየው እውቀት አነስተኛ መሆኑን ታዝቤ ነበረ። የሁለቱ መጻሕፍት ልዩነት እንደሚያስረዳው ሁሉ ይዞታው ለሌላ ጉዳይ ውሎ ቢገኝም ስለ እስላም ሃይማኖት የተባለውና በምእራፍ 5 ተሰብስቦ የሚገኘው ከ "ቅርጣሳማቲዎች" የተቀዳ መሆኑን ነው።

ስለ እስላም ሃይማኖት "ሐተታ ዘርአ ያዕቆብ" መጀመሪያ የሚያትተው /ከማግባት መመንኩስ ይሻላል የሚለውን የክርስትናን ሕግ ከወቀሰ በኋላ/ መሐመድ ስለፈቀደው ብዙ ሚስት ስለ ማግባት ሆኖ ከዚሁም የመሐመድ ነቢይነት ለማመን አስቸጋሪ እንደሆነ ግልጽነቱን ነው። ”የቅርጣሳማቲዎች" የመጀመሪያ ምእራፍ አንደኛው አንቀፅ የክርስቲያን ምንኩስናን ንፅህና አመስግኖ የእስላሞችን ብዙ ማግባት ነቅፎ ቁርዓን ራሱ በምዕራፍ 51 በቁጥር 49 የሚለውን የሚቃወም መሆኑን ለማሳየት ይሞክራል። "መፅሃፈ ዘርአ ያዕቆብ" ይህን

ቁጥር በመሰለው መንገድ ለስታቲስቲክስ ተጠቅሞበታል፡፡ ይህን አንቀጽ ሲጀምር "መፅሐፈ ዘርዓ ያዕቆብ" የመሀመድን ነቢይነት ሊያስረዱ የሚፈልጉትን የተአምርን ደራሲያን ይጠቅሳል፡፡ ይኸውም ነቢዩ ፈጽሞአቸዋል ተብለው በሱና የሚነገሩትን የሚያስተባብል በየቅርጣሳማቲዎች" በገጽ 101-103 የሚገኘው ግልባጭ ነው፡፡

በ"መጽሐፈ ዘርአ ያዕቆብ" በገጽ 11 የተጠቀሰው ስለ ባርያ ንግድ የሚናገረው ስለ እስላም ሃይማኖት ልዩ ሀሳቦች የተነገረው ሁለተኛው አርእስት ነው በ"የቅርጣሳማቲዎች" በምዕራፍ 11 የቀረበው ንግግርም ይኸው ነው* በኢትዮጵያው ጽሁፍ ስለ ሰው ልጆች ሁሉ ወንድማማችነት የተባለውም የዚህን የገደል ማሚቶ ቃል በቃል መስማት ይመስላል፡፡

ከዚህ ቀጥሎ አንድ የተወሰነ የምግብ ዓይነትን ብሉ አትብሉ በተወሰነ ቀን ብሉ አትብሉ የመሳሰሉትን ከንቱ ትእዛዛት እግዚአብሄር ሊሰጥ አይችልም ብሎ ካተተ በኂላ "መጽሐፈ ዘርአ ያዕቆብ እግዚአብሄር እስሰላሞችን በሌሊት እንጂ በቀን አትብሉ ሊል አችልም ብሎ ይከራከራል፡፡ "የቅርጣሳማቲዎች" በምዕራፍ 5 ያቀረበው ክርክርም ይህንኑ ነው፡፡ ከዚህ አንቀጽ ወዲያው ቀጥሎ በኢትዮጵያ ጽሑፍ የሚገኘው የስጋን ፍላጎት በማዳከሙ የፆም ሕግ መሰረት እንደሆነ የሚለው ክርክር የርእሰ ደብር ቡርጋድ አስተሳስብ ያነሳሳው ነው ለማለት ይቻላል፡፡

በእውነቱ "የቅርጣሳማቲዎች" በ"መጽሐፈ ዘርአ ያዕቆብ" ላይ ያለው ጠቅላላ ተፅዕኖ እንደተናገርኩት ሁሉ

ግልፅ ይመስለኛል። አንዳንድ ጊዜ ይሄ እነዚያን ለማሽነፍ መቅድም ሆኖ የቀረበና ከተቃራኒዎቹ እምነቶች ግጭት ሁሉም ከእግዚአብሄር የመነጩ አለመሆናቸውን ለማሳየት ቀርቧል ለማለት ይቻላል። ሁለቱንም መጻሕፍት በቅርብ በማነጻጸር ግንኙነታቸውን ከዚህ የበለጠ ዘርዝሮ ለማሳየት ይቻል ይሆናል። ይህ ግን የኢትዮጵያ ሥነ-ጽሁፍ ምርመራ ከመሆኑ ይልቅ የአባ ጁስቶ ዳ ኡርቢኖ ሥራ ምርመራ ይሆናል። "መጽሐፈ ዘርአ ያዕቆብ" በ17ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ይኖር የነበረ ኢትዮጵያዊ የፃፈው መሆኑ ቀርቶ በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ይኖር የነበረ የጣልያን መነኩሴ ልበ ወለድነቱን በብልሀት ሰውሮ የፃፈው መሆኑን የተባለው ሁሉ በብቃት የሚያስረዳ ይመስለኛል። በኛው ያዕቆብ ኡርቶፓሲ ነፍስ እንዴት ያለ ኀዘን ኑሮአል...ስለ ዳባዲ መጻሕፍት በጻፍኩት ዜና በእጁ ከጻፋቸውና ለፈረንሳዩ መንገደኛ ካደረገለት እርዳታ ገምቼ አስተያየቴን እንዲህ ስል ጽፌ ነበረ*

"ትሁት ሰው በተለይ የሚመራመሩት ሊቃውንት እንኳ ምንም ያህል የሚያውቁት ትጉ ተመራማሪ በጥናቶቻችን ታሪክ ውስጥ ለወደፊት ቦታውን የሚያገኝ "በዘመኑ ይኖሩ በነበሩት መረሳቱን የ"መጽሐፈ ዘርአ ያዕቆብ" እና ከዚሁም የ"መጽሐፈ ወልደ ሕይወት" ደራሲው መሆኑን በማወቅ ቂሙን የምወጣ መሆኔን መቸም አላስበውም ነበረ። ግን የ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ዕንቁ ይመስል የነበረው ከኢትዮጵያ ሥነ ጽሁፍ በንኖ ሲሄድ በማየቴ ከልቤ እያዘንኩ ነው።

## ዘርአ ያቆብ ኢትየጵያዊ ነው፡፡

### የኔታ አለማየሁ ሞገስ

የዓለም ስሙ ወርቄ፣ የጥምቀት ስሙ ዘርአ ያዕቆብ የሚባለው ኢትዮጵያዊ ከ1592-1685 የኖረ፣ በስሙ የታወቀውን የፍልስፍና መጽሐፍ የጻፈና ወልደ ሕይወት የሚባለውን ፈላስፋ አስተምሮ ደቀ መዝሙሩ ያደረገ ኢትዮጵያዊ ፈላስፋ ነው ተብሎ ታምኖ እስከ ቅርብ ጊዜ ነበር፡፡ አሁን ግን ኮንቲ ሮሲኒ እንዲህ ያለው የፍልስፍና መጽሐፍ ከኢትዮጵያውያን አይወጣም በሚል መንፈስ ተመስርቶ በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበረ ጁስቶ ዳ. ኡርቢኖ የሚባል ኢጣልያዊ ካቶሊካዊ መነኩሴ ነው እንጂ የጻፈው ኢትዮጵያዊ አይደለ ብሎ በሪያሊ አካዳሚያ ዲይ ሊንቼይ በ1920 በጣልያንኛ የጻፈውን አቶ በእምነት ገብረ አምላክ ወደ አማርኛ ተርጉመውት ባየው ማስረጃውንና ሀሳቡን ስለተጠራጠርኩ ነገሩን ሁሉ በውል ማጥናት ጀመርሁ፡፡

ከዚህም በላይ፣ በጠቅላላው አንድ ሕዝብ ታሪክ የለውም ማለት እንደ ጎረቤቶቹ የሰራውን ሁሉ በጽሑፍ፣ በሥዕል፣ በሕንፃ ለትውልድ የማሳለፍ ልማድ የለውም ማለት እንጂ በአለም ላይ አልኖረም ማለት ስላልሆነ፤ኢትዮጵያውያን አባቶቻችን ምን ምን እንደተውልን በሕንጻና በሐውልት እነአክሱምን እነላሊበላን እነፋሲል ግንብን ሌሎቹንም በየጠቅላይ ግዛቱ የሚገኙትን የታላላቅ አድባራት የሕንፃ ጥበብ በማስተዋል የዜማችንን ጣዕም፣የቅኔአችንን ርቀትና ጥልቀት፣የቅዱሳን መጻሕፍትን አተረጓጎም በማመዛዘን እንደገና እነዚህን ሁለቱን ሐተታዎች ባነብ

መንፈሳቸውም ሆነ ስራቸው ከቅድም ቅድም ኢትዮጵያዊ እየመሰለኝ ሄደ፡፡

ስለዚህም፣ ኮንቲ ሮሲኒ በጻፈው የሂስ ርእስ ያለው አልፎ አልፎ አጠራጣሪ ነገር ያለበት መስሎ ስለታየኝ ሐተታዎቹን ያነበብሁበት ጊዜም ዘግይቶ ነበርና እንደገና ዐረፍተ ነገሩን ሁሉ አንድ ባንድ እየተነተንሁ ዘለቅሁት፡፡ በመጽሐፉም ይዞታ መሠረት የተሰጡት ምክንያቶች ሁሉ በቂ ማስረጃዎች ስላልመሰሉኝ መጀመሪያ ይህን ሃሳብ ያመነጨውን ሰው ታሪክ ቀጥሎም ይህን ያለበትን ምክንያት ማጥናት አስፈላጊ መስሎ ታየኝና የጻፋቸውን ፅሁፎች ባነብ ከዐድዋ ጦርነት ወዲህ በጦርነት ባይሆን በብዕር የኢትዮጵያውያንን ስም ለማጉደፍ፣ የኢጣልያንን ለማወደስ የተነሳ ሰው መሰለኝ፡፡

ይህንንም ለመረዳት የሚከተለው ይበቃል፡፡

“on peut assurer que les etiopiens ne connaissent pas le haut genre depoexie. Ils n’ont guiere que le genre de la chanson.”

ይህን ከተናገረ በኋላ ደግሞ ዝቅ ብሎ ይህን ጽፉል፡፡

“je ne peut’ecrire que tr’es peu de choses surles regles de la bersififcation ‘etiopique”

ምንም ነገር የለበትም ከተባለ በኋላ አላውቀውም ማለት ተቃራኒ ነው፡፡

በሚከተለው ደግሞ ከዐድዋ ጦርነት በኋላ በኢትዮጵያ ላይ ከኛ ጠባይ ዝምድና የሌለው አንቀጽ ጽፎልናል፡፡

“Per di piu, per regioi storiche ed ambientali, la buona fede non era pianta

endemica in Ethiopia: le reserve mentali; la fedeviolata. I giuramenti rott-il non transmettersi, per consuertudini, gl'impegni da un re al suo successore indebolivano assai il trattato d' Uccialli.

ይህ አንቀጽ ስለ ውጫሌ ውል ከተነገሩት አስገራሚ አናቅጽ አንዱ ስለሆነ ፕሮፌሰር ሰበንፋቢንሰን ወደ እንግሊዘኛ ተርጉመውታል፡፡

"Moreover, for the hisrorical reasons and because of enviornmental conditions good faith was not a plant native to Ethiopa; the mental reservations, the violated trust, the broken oaths... the fact that obligations were not usually transferred from a king to his successor weakened the treaty of Ucciali very much.

ከዚህ አንቀጽ በኔ አስተያየት ሁለት ስህተቶች አሉ፡፡ በመጀመሪያ እምነትና ቀናነት የኢትዮጵያ ተወላጆች አይደሉም ብሎ ሕዝቡን እንዳንድ ሰው ለማጠቃለል ያስቸግራል፡፡ ቀጥሎም ግዴታዎች ከንጉሡ ወደ ወራሹ አለመተላለፋቸው የውጫሌን ውል አዳከሙት በማለቱ የውጫሌ ውል የተፈረመውና የፈረሰው በዚያው በአንድ ሰው በፀዔ ምኒልክ ሲሆን፣ ከፊተኛው ንጉሠ ነገሥት ካዔ ዮሐንስ ጋራ እንደተዋዋለ በማስመሰል አንባቢን አሳስቷል፡፡ ይህም እንደገና መጽሐፈ ዘርአ ያዕቆብን ለማጥናት አበረታታኝ፡፡ በዚህ ጊዜ የሮሲኒ ሐሳብ ሁሉ አጠራጣሪ መስሎ ታየኝ፡፡

ከዚህ ቀጥሎ በ19ኛው ክፍለ ዘመን የነበሩት ስለአፍሪካ የፃፉትን የአውሮፓውያንን ፀሀፊዎች በአያሌው አነበብሁ:: ለማሳየትም የሚፈልጉት፣ የአፍሪካን የመወረር ዘመን ስለነበረ ይህ ክፍለ ዓለም ከአውሮፓ ማነሱን በመሆኑ፣በገዛ ባህላቸው ተጠቅለው፣ አፍሪካ አላዋቂ ነው በሚል እምነት ታውረው ስለነበሩ በአፍሪካ ውስጥ የኪነ ጥበብን ዕድገት ለማየት አይችሉም ነበር:: ስለዚህ የ19ኛውን ክፍለ ዘመን የአፍሪካን ታሪክና የአውሮፓውያን ጸሐፊዎች የነበራቸውን አስተየየት ያጠናው ባሲል ዲበድሰን የሚባል ሰው የሚከተለውን ተናግሯል::

"There is bad history and good history. Bad history appears when historians allow their prejudice and feelings to get the better of them. Many imperialist historians of Africa, during the colonial period wrote bad history. Their prejudice and personal feelings made them write that the Africans had no history of their own. It is a part of the modern rebirth of Africa that these views to be entirely false.

እንደዚህ ያሉትን ካነበብሁ በኋላ ዘርአ ያዕቆብና ወልደ ሕይወት ኢትዮጵያውያን መሆናቸውን በዝርዝር ለማስረዳት ካስተማሪዬ ጋር ተነጋግሬ እንደ ምክራችን በምዕራፍ በምዕራፍ ዘርዝሬ ለማቅረብ ወሰንኩ::

ዳዊትንና ሰለሞንን ቃል በቃል መጥቀሱንና ሌሎቹን መጻሕፍት ብዙ ሀሳባቸውን አንዳንድ ጊዜም የራሱን ሃሳብ በእነሱ እያሳበበ መጥቀሱን በማሳየት

በሦስተኛው ከዛ የኢትዮጵያን ልማድና ባህል ያጣና የተቀኘ መሆኑን በመተንተን፣ በመቀጠልም አባ ጁስቶ በኢትዮጵያ የነበረበት ዘመንና ዕድሜው ለቅኔ ትምህርት በቂና ምቹ አለመሆኑን በመግለጽ፣በመጨረሻ ሮሲኒ የሰጣቸውን ምክንያቶች አፍርሶ፣ ማጠቃለያ ይሰጥና ይደመድማል።

ዳዊትና ሰሎሞን

በዚህ ምዕራፍ በኢትዮጵያ ዳዊት በቃል፣ቀጥሎም ሰሎሞን ብዙ ጊዜ ስለሚነበብና ስለሚጠቀስ ቃል በቃል መጥቀሱንን ሌሎቹን ግን በሃሳብ መጥቀሱንና አሳይቼ ፍጹም ኢትዮጵያዊ መሆኑን በማወዳደር አስረዳለሁ።

ስለዳዊት ያለው አስተያየት ከሊቃውንቶቻችን ጋር ይስማማል። የኢትዮጵያ ሊቃውንት ዳዊትን ሲሆን በቃላቸው ያለበለዚያም በመጽሐፍ ሳይደግሙ የዋሉ እንደሆነ ቅር ይላቸዋል። እሱም ካገሩ ሲሰደድ ይዞ የወጣው ዳዊቱን ነው። መጽሀፍ ቅዱስ በተናኘበት በዚህ ዘመን የነበረ የውጭ ሀገር ሰው ቢሆን ኑሮ በተጨማሪም ቢሆን መጽሐፍ ቅዱሴን በተቀረም ሐዲስ ኪዳኔን ይዤ በረርሁ ባለ እንጂ ዳዊቱን ባላለም። ለማስመሰል ነው እንዳይባልም ዳዊትን የጠቀሰው ቃል በቃል ነው።

“ወነሣእኩ ሠለስተ አውቅያተ ወርቅ ዘብየ ወመጽሐፊ ወመዝሙረ ዳዊት በዘአጼሊ ወኀ የይኩ ሌሊት ወኢከትኩ ወኢለመኑሂ ኀበ አይቴ አሐውር” ብኋል።

የሚጸልየውም ዳዊትን ነው። በሌሎቹ መጻሕፍት ላይ ሂሱን ሲያንጎደጉድ ክቡር ዳዊትን ግን አንድ ጊዜም

አልነቀፈም። የተሳሳተ መስሎ ሲታየውም የሚያስታርቅ ትርጉም ይሰጠዋል።

ዳዊትን የሚጠቅሰው ቃል በቃል እንጂ እንደሌሎቹ በሀሳብ አይደለም። ከዚህም በላይ ከዳዊት የተጠቀሱት ሁሉ በምዕራፍ ውስጥ የሚገኙ ናቸው። አብዛኛዎቹ በመስተጋብእና በክስተት የቀሩትም ሙሉ ምዕራፍ በሚባለው በደብረ ታቦርና በታላላቅ በዓለም በሚደረሰው ይገኛሉ። ይህም የሚያሳየው ምንም ድምጹ ዝግ ቢሆን በልጅነቱ በታላላቅ በዓላት ከደብር አለመለየቱን ነው። ስለዚህ በዜማ በኩል ባይማርም ያዳምቅ ነበረ ለማለት ይቻላል። በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ያላደገ እነዚህን ጥቅሶች በቃሉ ያውቃል ለማለት በጣም ያዳግታል።

አለማየሁ ሞገስ ዘርአ ያዕቆብ የኢትዮጵያዊ ሰው ለመሆኑ ዳዊትን እንዴት አስተካክሎ እንደሚጠቀስ፤ስለምንን ጥቅሱን ለማስገባት እንዴት አተራምሶ እንደሚጠቀስ የግዕዙን ምሳሌዎች በመስጠት በሚገባ አብራርተዋል። ከዚህም ሌላ ከሁለቱ መፅሀፍት ውጭ ያሉትን ጥቅሶች ግን ሀሳባቸውን እንጂ ቃል በቃል ለመጥቀስ እንዳልሞከረ ተንትነው ይህም የኢትዮጵያ ሊቃውነት ከዳዊት ጋር ያላቸውን ቁርኝት የሚያሳይ መሆኑን ስለሚጠቁም የዘርአ ያቆብም በተለይ ዳዊቱን መውደዱ ለኢትዮጵያዊነቱ ዋና ምስክር እንደሆነ ያትታሉ።

## የጁስቶ ዳ ኡርቢኖ ዘመን ለቅኔ በቂ አይደለም

ይህን መፃፍ የሚችል ቢያንስ ከዜማ ቅኔ ቤት ከመግባት በፊት የሚሰጡትን የቃል ትምህርትና ጸመ ድጓ የዘለቀ፣ አማርኛንና ግዕዝን ያወቀ፣ በቤተ ክርስቲያናችን ያደገ፣ባህላችንን ያጠና ቅኔ በደንብ ያወቀ መሆን አለበት።

ዳ ኡርቢኖ በኢትዮጵያ የኖረበት ጊዜ ይህን ሁሉ ለማጥናት በቂ አይደለም። በኢትዮጵያ የቆየው ስምንት ዓመት ሲሆን በራሱ ደብዳቤ መሠረት ለጥናት ያደላው ግን ሦስት ዓመት ብቻ ነው። ከዚህ ደግሞ አንዱን ለመጽሐፉ መጻፊያና መላኪያ ብንቀንስ ሁለት ዓመት ብቻ ይቀሩናል። በእነዚህ ወራቶች አማርኛና ግዕዝ አጥንቶ ቅኔ ተቀኝቶ እንዲህ ያለ መጽሐፍ ለመጻፍ ቻለ ለማለት አዲስ ተአምር ማንበብ ይሆናል።

ዕድሜውና ዘመኑ ለጁስቶ ዳ ኡርቢኖ የቅኔ መማሪያ በቂና የተመቸ እንዳልሆነ ራሱ ሮሲኒ የሚተርከው ይበቃናል። በእሱም የምናነበው የሚከተለውን ውጤት ይሰጠናል። የሚወዳት ልጁ ብትሞትበት የመነኮሰ እንጂ ከልጅነቱ በፍልስፍና እየተራቀቀ ያደገ አይደለም። ከተራ ደብዳቤዎች በቀር በልብ ወለድና በታሪክ ጽሁፍ እንኳ የታወቀ አይመስልም። የእነዚህ ተወዳዳሪ የሚሆን ሌላ መጽሐፍ ጽፎ በሕይወቱ አሳትሞ አላወጣም። ችሎታው በግዕዝም ሆነ በአማርኛ የት ድረስ እንደነበረ የሚገልጥ በቂ ጽሁፍ አልተገኘም። በሚስዮን እያገለገለ የሐዋርያት ወይም የሰማዕትነት ዋጋውን እስከ መጨረሻው ሲጠብቅ ኑሮ ሞተ እንጂ አንድም ቀን ከክርስቶስ መንገድ ዘባ አላለም።

ሰውዬው እንዲህ ያለ ሲሆን ኮንቲ በ31 ዓመቱ በአንድ ዓመት ፈረንሳይንና ዐረብን ዐጠና ብሎ ታምረኛ ሰው አድርጎ ይነግረናል። ጊላም ከስራው ጋር መጽሐፍ እንደ ልብ በማይገኝበት፣ ዘመኑ ሰላም ባልነበረበት፣ በዚያን ጊዜ በዓመት ተመንፈቅ ገደማ ግዕዝን ተምሮ የሀገሩን ባህል አጥንቶ ሐተታ ዘርአ ያዕቆብን ወልደ ሕይወትን የመሰሉ መጻሕፍት አበረከተ ይላል። ዳ ኡርቢኖ በኢትዮጵያ የቆየው ስምንት ዓመታት ብቻ ነው። ይህም ሮሲኒ እንደሚለው ከ1847-50 ከስብከት በቀር በጥናት በኩል ምንም አልሰራም። በ1855 ከሀገር ወጣ። ከ1850-52 ባሉት ወራቶች ውስጥ ነው ቋንቋውንና ባህሉን አጥንቶ እንዲህ ያለ ጽሑፍ ጻፈ የተባለው ማጥናት የጀመረበት ዘመን የካቲት 17/1850 መሆኑን የሚገልጥ ደብዳቤ በኢጣልያ ለነበረው ወዳጁ የምስራው ስለሌለም ያገሩን ቅዱስ ቋንቋና ድርሰት ማጥናት ጀመርሁ አሁን ብሎ ጽፏል።

ይህን ደብዳቤ በጻፈ በሦስት ዓመቱ በየካቲ 28/1853 ለአንቷን ዳ ባዲ ከደብረ ታቦር በጻፈው ደብዳቤ ካመታት በፊት አንድ የተቀደደ መጽሀፍ ማየቱንና በጊላም ሙሉውን መጽሐፍ ወደ ደንቢያ ዘምቶ ከተመለሰ ወታደር እንደገዛ ይናገራል።

በእነዚህ በሦስት ዓመታት ውስጥ በዚህ በሃይማኖት ምክንያት መምህራኑ ይጣሉበት፣መጽሐፍና አስተማሪ እንደልብ በማይገኝበት ሃይማኖት ለማስተማር ተልኮ የመጣ ከበላዩ ተቆጣጣሪ ያለበት፣ በ40 ውስጥ ያለ፣ ከዚህም በላይ ዐይነ ሕመምተኛ ሰው አማርኛና ግዕዝ ተምሮ አንድም ጽሁፍ የሌለውን የሀገሩን ባህልና

ይትበሃል በሁለት ዓመት አጥንቶና እንዲህ ያለ መጽሐፍ ጻፈ ማለት ለኔ ተአምር ስለሚመስለኝ ፍርዱን ለአስተዋይ አንባቢ እተዋለሁ፡፡

መጽሐፉ በጠቅላላ የተመሰረተው በቅኔና በመጽሐፍ ቤት በሚተርከው ታሪክ መሰረት ነው፡፡

ስለ ባዕዳን ሃይማኖታት ይናገራል፡፡ ይህም ተማሪ ማለዳ ማለዳ ለስምና ለወርቅ ማፍሰሻ እየተባለ የሚተረክለት በትርጓሜ መጻሕፍት የታወቀ በስንክሳርና በገድለ ቅዱሳን የተጻፈ ነው፡፡

## ለኮንቲ ሮሲኒ ምክንያት ቀጥተኛ መልስ

ኮንቲ ሮሲኒ በእነ ዘርአ ያዕቆብ ላይ ያቀረበውን የሂስ ጽሑፍ መርሕ በማድረግ ልክ እሱ እንዳቀረበው ለምክንያቱ ሁሉ መልስ እሰጣለሁ፡፡

ሀ/ "የቅዱሳት መጻሕፍት አተረጓጎም የቁስጥንጥንያን አተረጓጎም የተከተለ በመሆኑ ለነጻ አስተሳሰብ ማለፉ ምናልባት የማይቻል ክልል በመሆኑ በኢትዮጵያ እንደ ምን ታለመ ብሎ ማሰብ እንኳ አዳጋች ስለሆነብን የዘርአ ያዕቆብ ናቸው የተባሉት ሃሳቦች ከኢትዮጵያ የሚጠበቁ አልነበሩትም፡፡"

በዚህም በፍልስፍና አይፈላሰፉም፣ አምላክን አይጠራጠሩም፣ የሃይማኖታቸው ሥርዓት ብቻ የሚያዝዛቸውን ተከትለው ያልፋሉ ማለቱ ነው፡፡

ሕዝብ አንድ ሰው አይደለም፣ ጻድቅ፣ኃጥእን፣ ሌባ፣ ታማኝ፣ደግ፣ክፉ፣አጭር ረጅም ብልህ፣ ቂል፣ ኀያል፣ ደካማ ሁሉም በያይነቱ ይገኝበታል፡፡ ሕዝብን እንዳንድ ሰው አድርጎ ለመናገር በፍጹም አይቻልም፡፡

አጠቃልላለሁ የሚል ደራሲም በአንባቢ ዘንድ ትዝብት ማትረፉ አይቀርም።

ማንም ሳይረዳቸው በራሳቸው ትርጓሜ መጻሕፍትን በቋንቋቸው ከባህላቸው ጋራ አስማምተው ለሀዘንና ለደስታ መግለጫ ልዩ ልዩ ዜማ እያወጡ፣ በሌላ ሀገር የሌለ የቅኔ ቤትና ድርጅት አቋቁመው የኖሩ የኢትዮጵያ ሊቃውንት አያውቁም፣ አያስቡም የሚባሉ በማያውቃቸው ነው። እንደዚህ ያለውን ኢትዮጵያውያን አያስቡም ያሰኘ ዘርአ ያዕቆብስ አንዱን አምላክ ይዞ እያመሰገነ ነው የሚሄደው፣ቢነቅፍም ሃይማኖትን በስህተት ያስተማሩትን ልዩ ልዩ የታላላቅ ሃይማኖት መሪዎችን ነው። የእኛ ሊቃውንትና መሪዎችስ ከዚያም አልፈው ተርፈው ራሱን ፈጣሪያቸውን ሲነቅፉ ሲሳደቡ ኑረዋል።

ለዚህ ማስረጃ ኮንቲ ሮሲኒ ከመወለዱ በፊት የተፃፉና የታተሙ ብዙ ቅኔያት አሉ። (በግዕዝ ምሳሌ ሰጥተዋል)

በ18ኛው መቶ ዘመን በጎንደር የሠርክ ጎብስት ሕግ በተስፋፋበት ጊዜ አንድ ደቀመዝሙር ሳዶቅ የሚባል ጎንደሬ ቢያናድደው የእግዚአብሔርም ኩነኔ በፍርድ መሆን አለበት በማለት የተናገረውን ለአብነት መጥቀስ ይቻላል።

ከዚህም በላይ ተከታይ እያጡ ነው እንጂ እንኳንስ የሃይማኖትን መስራቾች መንቀፍ ክርስቶስ እኔ ነኝ እያሉ ሲነሱ የኖሩም ብዙ ናቸው።

ጥንት እኔ ክርስቶስ ነኝ ብሎ የተነሳ እንደነበርና በጊዜውም ሰቅለው እንደገደሉት ከሱ ጋራ ሰባት መቶ ሰዎች እንደሞቱ የሚነገር አፈ ታሪክ አለ።

ይህ ሰው ከዚህ በፊት የመጣው በሥጋ በመወለድ ቀደመኝ እንጂ እኔ ትልቁ ነኝ እያለ ሰብኳል። ይህም ሌላው ይቅርና አምላክ ነኝ እያሉ የተነሱ ኢትዮጵያውያንም እንደነበሩ ያስረዳል።

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ምሳሌዎችና ታሪክ ከኢትዮጵያውያን በፍልስፍና ዓለም እንዴት እንደነበሩ ከማሳየታቸውም በላይ እንዲህ ያለው ከኢትዮጵያውያን የሚጠበቅ አይደለም ያለውን ምክንያት በደምብ ማፋረሳቸውን ገልጬ ግምቱን ለአንባቢ እተዋለሁ።

ለ/ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ መጻሕፍቱ አብረው ተጠርዘው ከተገኙ ያንድ ሰው ናቸው ብሏል። ይህም በሃሳብ የሚቀራረቡትን ሰማንያ አሃዱ የቤተ ክርስቲያናችን መጻሕፍት ባንድ ተጠርዘው ቢያይ አንድ ደራሲ ነው የደረሳቸው እንደ ማለት ነው።

ኢትዮጵያውያን መጻሕፍትን አብረው የሚጠርዙት ለልዩ ልዩ ሌላ ጉዳይ ነው እንጂ በአንድ ደራሲ ተደረሱ ለማለት አይደለም። ምክንያቱም አንደኛ ለመያዝ እንዲመቹ፤ ሁለተኛ ለማዛመድ ነው። ለዚህም የሚከተሉት አብረው የተጠረዙት መጻሕፍት ያስረዱናል።

1/ በዓለም የታወቀ ራሱ መጽሐፍ ቅዱስ።

2/ በየጊዜው ከዳዊት ጋር ሲጻፉና ሲታተሙ የኖሩት የፀሎት መጻሕፍት ከታተሙት በ1941 ዓ.ም በተስፋ ገብረሥላሴ ማተሚያ ቤት

የታተመውን ዳዊት መጥቀስ ይበቃል። እሱም ዳዊት፣ፀሎታት ዘዐሠርቱ ወሃምስቱ ነቢያት፣ መኀለየ ሰሎሞን፣ ውዳሴ ማርያም፣ አንቀጸ ብርሃን ቅዳሴ ማርያም፣ እና መልክአ ኢየሱስን ይዟል። የሚከተሉት ደግሞ አንድነት ተጠርዘው በብሔራዊ ቤተ መጻህፍት ወመዘክር አዲስ አበባ ይገኛሉ።

3/ መልክአ ጉባኤ፣ /የስማዕታት የጻድቃን የመላእክት መልክአት/

4/ መልክአ ገነት ጽጌ በኋላ መልአከ ብርሃን "መጽሐፈ ታሪክ" በሚለው መጻፉቸው የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ ሰብስበው ጠርዘዋል። የተሰበሰቡትም፤

ሀ/ ታሪክ ከቀዳማዊ ምኒልክ እስከ ግራኝ ባጭሩ

ለ/ ግሥ

ሐ/ 45 ልዩ ልዩ መልክአት።

መ/ ገድለ አቡነ አረጋዊና ገድለ ገብረ መንፈስ ቅዱስ፤

ሠ/ ገድለ ሐዋርያት፣ ጴጥሮስ ጳውሎስ፣ ስምዖን ያዕቆብ፣ እንድርያስ በርቶሎሜዎስ ቶማስ ማቴዎስ ሉቃስ ፊልጶስ እንድርያስ ረድእ፣ ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ፣ ያዕቆብ ወልደ አልፍዮስ፣ማትያስ፣ያዕቆብ ወልደ

ነጉድጓድ፣ ማርቆስ፣ ቶማስ ሐዋርያ፣ ታዲዎስ።

5/ ከመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ አ.እ. ቤተ መጻሕፍት ያለ ቅዳሴ ደግሞ፣

ሀ/ ሙሉ ቅዳሴ፣ ለ/ ታሪክ፣ ሐ/ ሥርዐተ ቤተ ክርስቲያን፣

መ/ ሥርዐተ ቅዳሴ ይዟል

6/ ሌላው ደግሞ

ሀ/ አቡሻክር /መርሐ ዕውር/

ለ/ መቅድመ ወንጌል

ሐ/ ቀለምሲስ

መ/ ዕዝራ ሱቱኤል

ሰ/ ታሪክ አብያተ ክርስቲያናት።

ረ/ መልእክተ አበው

ሠ/ ታሪክ መናፍቃን

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት መጻህፍት የመጻሕፍት አብሮ መጠረዝ ባንድ ደራሲ የተደረሱ ለመሆናቸው ማስረጃ ለመሆን አለመቻሉን ይገልጣሉ።

ሐ/ ከዚህ ቀጥሎ የተሰጠው ምክንያት ደግሞ የእጅ ጽሁፍ ነው።

የእጁ ጽሁፍ በ17ኛው ወይም በ18ኛው ክፍለ ዘመን መሆኑ ቀርቶ የ19ኛው ክፍለ ዘመን መስሎ በማግኘቴ በጣም ተገረምሁ ብሏል።

አባ ጁስቶ ዳ ኡርቢኖ ራሱ በገዛ ደብዳቤው መጀመሪያ የተቀደደ በኋላ ሙሉውን ማግኘቱን መስክሯል። በኋላ ግን የፈለገውን ያህል ሊገለብጠውም

ሊያስገለብጠውም ስለሚችል፣ እኔ ያገኘሁት መጽሐፍ የእጅ ጽሁፍ የዚህ ዘመን ነው ለማለት እንጂ መጽሐፉ የተደረሰው በዚህ ዘመን ነው ለማለት አያስችልም። መጻፉ ራሱ ብዙ ጊዜ ተቀድቻለሁ እያለ እኔ የያዝሁት ቅጅ ያሁኑ ዘመን ስለሆነ መጽሐፉም በአሁኑ ዘመን ነው የተጻፈ ማለት፣ ሐዲስ በዚህ ሰሞን በእጅ የተፃፈ ኦሪት ይዞ በዚህ ሰሞን ነው የተደረሰች ከማለት አያንስም።

መ/ መጽሐፉ ብዙ ቅጅ የለውም ብኋል። ብዙ ቅጅ ስላለው ኢጣልያዊ ነው የጻፈው ወይንም ኢጣልያዊ ስለጻፈው ነው ብዙ ቅጅ የሌለው ማለት ልከኛ አስተሳብ መሆኑና አለመሆኑን ለአንባቢ ልተውና፣ ምክንያቱን ልናገር።

መጻሕፍቱን እንዳይራቡ ያገዳቸው እንቅፋት፣

ሀ/ ራሳቸው ደራሲያኑ ፈሪዎችና አድርባዮች ስለነበሩ፤ በመጽሐፉ እንደታታተመው በምስጢር ይዘዋቸው ኑረዋል። ለ/ የጻፈውና ያጻፈው የሚል ቃል ኪዳን የሌለው መጽሐፍ የማባዛት ዕድል በሀገራችን አልነበረም። የሃይማኖት ባለመሆናቸው ጠፍተዋል እንጂ መጀመሪያ ብዙ ቅጅ እንደነበራቸው ራሱ ኮንቲ በሰበሰባቸው ደብዳቤዎች አባ ጁስቶ መጀመሪያ የተቀዳደ፣ በኋላ ሙሉውን ማግኘቱንና መግዛቱን ሲናገር በብዙ መኖሩን ገልጧል።

ስመ ጥፉው ካቶሊክ ካህን አባ ተክለሃይማኖት፣በአባ ጁስቶ ስማቸው ከተጠራው ከቤተልሔሙ ደብተራ አማርኸኝና ከሊቀ ካህናት ጎሹ ጋራ በበጌምድር በነበረበት ጊዜ ፍራማሶን የተባሉትን የከሐድን መጥፎ ትምህርት ያለበትን አንድ መጽሐፍ

ገዝቶ አባዛቶ ለወላጆቹ ሰጠ ብሎ መግዛቱንም ማባዛቱንም መስክሯል፡፡

ለምስሐበ መናፍስት እየተባሉ የተደረሱ ብዙ ድርሰቶች በሀገራችን እንዳሉ የተረጋገጠ ነው፡፡ ግን የሃይማኖት ስላልሆኑ በብዙ ተራብተው አይገኙም አይሰጡም፡፡

ሠ/ የደቀ መዝሙሩ መጽሐፍም በእንፍራዝና ባቅራቢያዋ በሚገኙት በበጌምድር አውራጃዎች አንድ ትምህርት ቤት በውነቱ አቋቁሞ ትምህርት ቤቱ ለጥቂት ጊዜ የቆየ መሆኑን በገለጠልን ብኋል፡፡

ሁለቱም ሀሳባቸው ለትውልድ ጽፈው ለማለፍ የሚፈልጉ ፈላስፎች እንጂ ለሃይማኖታቸው ሲሉ ጽዋትወ መከራን አልፈው የሰማዕትነት አክሊል ለመቀበል የተዘጋጁ ሐዋርያት አልነበሩም፡፡ በማስተማርም ከሆነ ራሱ ጄስቶ ዳ ኡርቢኖም አላስተማረውም፡፡

ረ/ ሞክሼነት፣

"ከሁሉ አስቀድሞ ያዕቆብ መሆኑን ያመላከትሁት፣ ራሱ ያባጄስቶ የክርስትና ስም ከሐተታው፣ ደራሲ ጋር ይገናኛል፡፡"

ይህም ማስረጃ ነው ተብሎ የሚቀርብ አይደለም፡፡ በምዕራባውያን የክርስትና ስም በጣም የተወሰነ ስለሆነ በቤተ ዘመድ ስም ካልሆነ ከቤተሰቡና ከቅርብ ወዳጆቹ በቀር በዚህ የሚጠራው የለም፡፡ ይልቁንም ዮሐንስ ያዕቆብ፣ ጴጥሮስ ጊዮርጎስ በጣም ርካሽ በመሆናቸው አንዳንድ ምዕራባዊ ቋንቋ ያጠና ሁሉ ያውቀዋል፡፡ ከዚህም በላይ ያዕቆብና ዘርአ ያዕቆብ ፍጹም

ሞክሼ አይደሉም:: በክርስትና ስም ሞክሼነት መጽሐፍ ለፈረንጅ የሚሰጥ ከሆነ የኔም የጥምቀት ስም ጳውሎስ ነው:: ስለዚህ መጻሕፍቴም በሺ ለሚቆጠሩ ምዕራባውያን ሊሰጡ ይችላሉ:: ከዚህም ሌላ የማይገባኝ ከ17ኛው እስከ 20ኛው ክፍለ ዘመን ብዙ የክርስትና ስማቸው ያዕቆብ የሚባሉ ፈረንጆች ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ነበር:: እነርሱም ያዕቆብ ብሩስ (James Bruce) ያዕቆብ ፊትሎቢች (jaques Fatlovitch) ያዕቆብ ፓርክ (James Park) ያዕቆብ ባርት (James Barth) ከእነዚህ ሁሉ ለምን አባ ጁስቶ ዳ ኡርቢኖ ተመረጠ ለዚህ ጥያቄ መልሱ ኢጣሊያዊ በመሆኑ ነዋ! ለማለት ይቻላል:: በዚህም ሮሲኒ ከኢጣልያዊ በቀር በረቂቅ ፍልስፍና የሚፈላሰፍ የለም ለማለት በኢርቱዕ ሞክሯል:: የዚህ ሀሳብ እውነትነት እስከየት እንደሆነ ግን የፍልስፍናን ታሪክ የተማረ ሁሉ ስለሚያውቀው እኔን አያሳስበኝም::

ለ/ ስለባእዳን ሃይማኖታት፣

ስለዚህ በአራተኛው ምዕራፍ ላይ ተጽፏል::

ቀ/ የቃርጣጎና ታሪክ ተፅዕኖ በዘርአ ያዕቆብ ላይ ይገኛል ብሏል:: እነዚህም ተቃራቢ ስሜት የያዙ ዐረፍተ ነገር እንጂ በቂ ማስረጃዎች አይደሉም:: ከዚህም በላይ ዘርአ ያዕቆብ የቃርጣጎናን ታሪክ አይቶት ቢሆን ኑሮ እንደ ልማዱ በከመ ይቤ እያለ ይጠቅሰው ነበር እንጂ ባልሸሸገም:: እንዲያውም እንዲህ ያለ ፈላስፋ ሌላም አለ እያለ ጓደኛ እንዳለው ማውራቱ ከመደበቁ በተሻለ ነበር:: ያም ሆነ ይህ መጻሕፍቱ ይመስላሉ ተብለዋልና ለሁሉም መልስ እሰጣለሁ::

በቃርጣን ታሪክ ከገጽ 101-3 የተጻፉት በጣም ተራ ነገሮች ስለሆኑ ማንም ያወረቻዋል። ዘርአ ያዕቆብም በአካባቢው የሚወራውን ቢያወሳ ገለበጠ አያሰኘውም። እስልምና በዐረቢያ የመንግሥቱ ሃይማኖት ከመሆኑ በፊት የመሀመድ ተከታዮች ወደ ኢትዮጵያ ሸሽተው በአክሱም ቤተ መንግስት ብዙ ዓመታት እንደ ቆዩ የኢትዮጵያና የእስልምና ታሪክ ይናገራል። በአጋሚ አውራጃ መስጊዱ የሚገኘው የመሀመድ ነጋሽ ታሪክም እስልምና በኢትዮጵያ የተስበከው ዛሬ በእስልምና ከሚኖሩት ሀገሮች በፊት መሆኑን ያስረዳል። በአክሱም የእስላም ነጋዴዎችና ሸሖች ከጥንት ጀምረው መኖራቸው አይካድም። ስለዚህ ተመሪማው ዘርአ ያዕቆብም ከእነሱ ጠይቆ በቀላሉ ሊረዳ ይችላል።

በ/ የቃርጣን ታሪክ ቀድሞ ቢሆን ኑሮ የመጽሀፉን ሀሳብ የሚደግፉ ለምስክርነት ያህል እንኳ ብዙ ነገሮች ይጨምሩ ነበር።

ተ/ ሴት ማብዛት ሴት መቀነሱን ዘርአ ያዕቆብ የተማረው ከቃርጣንን ታሪክ መሆኑን ለማስረዳት ሞክሯል። ሴት ማብዛት ሴት መቀነስ እንደሆነ የማያውቅ ኢትዮጵያዊ በብዙ ያለ አይመስለኝም። ጥበበ ሲራክ ወደ ግዕዝ ከተተረጎመበት ጊዜ ጀምሮ፣

ኀ/ ስለባርያ ንግድም ያወቀው የቃርጣንንን ታሪክ አንብቦ ነው። ብሏል።

ይህን በዓለም የታወቀ፣በብሉይና በሐዲስ የተጻፈ በሀገራችንና በመካከለኛው ምሥራቅ እንደ ዕቃ ሸያጭ ተቆጥሮ አስተዋዩን ሰው ሁሉ ከ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በፊት ሲያሳስብና ሲያጨቃጭቅ ኑሯል። ይህንንም

ዘርአ ያዕቆብ ቢያወሳ ከቃርጣንን ተውሶ ነው ተብሏል። ይህስ ራሱ በጣም ግልጥ በመሆኑ ጥናት ስለማያሻው ለአንባቢው ፋንታ እተውለታለሁ።

ነ/ ምግብንና ጾምን ግዝረትን የመሳሰሉትን ኢትዮጵያዊ አንብቦ እንዳልተረዳቸውና አቶ ወርቂም ከቃርጣን ምሽቶች የተዋሳቸው አስመስሎ አቅርቧል።

እነዚህ ምግባሮች በኢትዮጵያ በየጊዜው እየተነሱ ሕዝቡን ሲያከራክሩ መኖራቸውን ማንም ያውቃል። ይልቁንም ከአሥራ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ወዲህ ጥዋት ማታ የሚያወዛግቡ ሁነዋል። ከዚያውም አጼ ገላውዲዎስ የኢትዮጵያን እምነት የሚያስረዳውን ጠማራቸውን ከጻፉ ወዲህ እነዚህን የማያውቅ ሊቅ በከተማው አካባቢ አልነበረም።

አ/ የፆም ሕግ መሰረቱ የሥጋን ፍላጎት ለማድከም ነው። የሚለው ክርክር የርዕስ ደብር ቡርጋድ አስተሳሰብ ያነሳሳው ነው ለማለት ይቻላል በማለት ከቃርጣን ምሽቶች የተወሰደ ሀሳብ አስመስሎ አቅርቦታል።

ይህም የመጣው ከፍትሐ ነገሥት፣ አንቀጽ በእንተ ኩሉሙ አጽዋም ከሚለው ነው።

በእነዚህ ምክንያቶች ነው እንዲህ ያለው ከኢትዮጵያውያን አይጠበቅም የተባለው።

## ማጠቃለያ

ሐተታ ዘርአ ያዕቆብን የጻፈው ቢሆን ዘራፊ የነበረ ቢያንስ የተቀኘ ቅኔ ዐዋቂ ሰው ነው። ዳዊትን በደንብ ያውቃል፣ ሰሎሞንን አንብቧል። የቀሩትን መጻሕፍት ግን አንብቧቸው ተረስተውት ወይም በጆሮ ጠጋብነት እንደሆነ የሚጠቅሳቸው አይታወቅም። አንድ ጊዜ የመጽሐፉን ሃሳብ በሌላው ጊዜ ደግሞ የራሱን በመጻፉ አስቦ በከመይቤ እያለ ሳያስተካክል ይጠቅሳል። ላቲን ይል ጣልያን ወይንም ፈረንሳይ አያውቅም። የሀገራችንን ሰው ለልምዱ ቀናዒነቱን በደንብ ያውቃል። ባህላችን አጥንቷል፣በልማዳችን ኑሯል። ስለዚህ የሀገሩን ባህል ነክቶ ከሰው እንዳይጣላ ፍልስፍናውን በድብቅ ጽፎ ላንድ ሰው ብቻ አስተምሮ አልፏል። ፍልስፍናውን ለመጭው ትውልድ እንዲተላለፍለት የሚፈልግ እንጂ እምነቱን አስተምሬ ሀሳቤን ገልጬ ልሙት የሚል ሃሳብ አልነበረውም።

በጥናታችን መሰረት ዘርአ ያዕቆብ ይህ ሲሆን አባ ጅስቶ ዳ ኡርቢኖ ደግሞ እንደሚከተለው ነው። እስከ 31 ዓመቱ ዓለማዊ ሆኖ ኑሯል። በዚህ ጊዜ ግን የሚወዳት ልጁ ስለሞተችበት ወደ ቤተክህነት ትምህርት ተዛውሯል። ጠበቅ ያለ ሥራ አይወድም። ካንዱ ስራዊት ወደ ሌላው ይዘዋወራል። ይህን ጠባዩን ይዞ ወደ ኢትዮጵያ ሚስዮን ይላካል ሲሉት ጊዜ አባ ማስያስን ተከትሎ በ1847 ዓ.ም መጥቷል። የሚስዮን ሥራውን እየሰራ በሀገራችን ለ8 ዓመት ቆይቷል። ግዕዝንና አማርኛን ለማጥናት ያዘነበለው ከ1850-1853 ነው። ግዕዝን ይወዳል፣ ግን ጊዜ በማጠሩ ምክንያት አጣርቶ

ለማወቁ አይከድም። የላቲናውያን ቀሳውስት አነጋገር ተዕዕኖ አልለቀቀውም ነበር። የሃገሩን "ቅዱስ ቋንቋ" ይላል። የካቶሊክን ሃይማኖት ለማስተማር የተዘጋጀ የስማዕትነት አክሊልን ለመቀዳጀት የሚጣባበቅ እሙን መነኩሴ ነበረ።

1995 አዲስ አበባ

መታሰቢያ

እነዚህ መጽሐፍት መታሰቢያነታቸው ለዘርአ ያዕቆብ ኢትዮጵያዊነት ሽንጣቸውን ገትረው ለተከራከሩ እና አለምን ላሳመኑ ኢትዮጵያውያንና አፍቃሪ እውነት ለሆኑ የአለም ሰዎች ሁሉ ይሁን፡፡፡